# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ | 83ኛ ዓመት ቁጥር 175 የካቲት 25 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!















# በ132 ሺህ ጣቢያዎች ችግኞችን የማፍላት ሥራ እየተከናወነ ነው

## - ዘንድሮ 6 ነጥብ 5 ቢሊዮን ችግኞች ይተከላሉ

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ለዘንድሮው አረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር ከ132 ሺህ በላይ የችግኝ ጣቢያዎች መዘጋጀታቸውን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ ስድስት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል መታቀዱም ተገልጿል፡፡

በግብርና ሚኒስቴር በተፈጥሮ ሀብት ልማት ዘርፍ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም መሪ ሥራ አስፈጻሚ ፋኖሴ መኮንን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ለዘንድሮው የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር ከ132 ሺህ በላይ የችግኝ ጣቢያዎች ተዘጋጅተው ችግኞች እየተፈሉ ነው፡፡

ለዘንድሮው አረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር በ132 ሺህ 144 ችግኝ ጣቢያዎች ተዘጋጅተው ችግኝ እየተለማባቸው ነው ያሉት አቶ ፋኖሴ፤ በመርሐ ግብሩ በሀገር አቀፍ ደረጃ ስድስት ነጥብ አምስት ቢሊዮን የተለያዩ ችግኞችን ለመትከል ታቅዷል ብለዋል፡፡

ችግኝ ጣቢያዎች በማኅበራት እና በመንግሥት ፕሮጀክቶች ተደግፈው አቅማቸውን እንዲያሳድጉ እየተሠራ መሆኑንም ገልጸዋል።

ከ 132 ሺህ በላይ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# የቀጣናውን ሀብት በጋራ የመጠቀም ጥረት

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

**ዜና ትንታኔ**

ኢትዮጵያ ከጎረቤቶቿ ጋር የእርስ በእርስ ግንኙነት ለማዳበርና ሰጥቶ የመቀበል መርሕን እውን ለማድረግ ሰፊ ዕድሎች አሏት። በአካባቢው የሚገኙ ሀብቶች በጋራ መጠቀም አብሮ ለመበልጸግ እንዲሁም ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች በመፍታት ቀጣናዊ ትስስር ለማሳደግ የሚኖረው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡

ምድረ ቀደምትነቷ፣ ያላት ታሪክና ቅርስ፣ የዲፕሎማሲ ፅኑ አቋም፣ የጂኦ-ፖለቲካል አቀማመጥ፣ በቀጣናው ያላት ተፅዕኖ ፈጣሪነት፣ ከጎረቤቶቿ ጋር የሚያስተሳስሯት ማኅበራዊ መስተጋብሮች እንዲሁም ለአፍሪካ ሀገራት ያበረከተችው ነፃነት በቀጣናው የሚገኙ ሀብቶች በጋራ የመጠቀምን ዕድል የሚያሰፉ ጉዳዮች ናቸው፡፡

ኢትዮጵያ የባሕር በር ለማግኘት ታኅሣሥ 22 ቀን 2016 ዓ.ም ከራስ ገዟ ሶማሌ ላንድ ጋር የተፈራረመችው የመግባቢያ ሰነድ በቀጣናው የሚገኙ ሀብቶች በፍትሐዊነት የመጠቀምና ሰጥቶ መቀበልን መርሕ ያደረገ መሆኑን አሳውቃለች። ነገር ግን ከጋራ ተጠቃሚነት ይልቅ የራሳቸውን ጥቅም ብቻ ከግምት ውስጥ የሚያስገቡ አካላት በራሳቸው መንገድ



ትርጉም እየሰጡት ይገኛሉ፡፡

ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያላት ትስስር በሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ይበልጥ በማሳደግ የባሕር በር ለማግኘት ልትጠቀምበት ይገባል ሲሉም ምሑራን ይናገራሉ፡፡

ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ቆይታ ያደረጉት፤ ረዳት ፕሮፌሰር አደም ካሚል፤ ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገራት ጋር የሚያስተሳስሯት ጉዳዮች በሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት በማሳደግ የባሕር በር ለማግኘት መጠቀም ትችላለች ይላሉ።

ኢትዮጵያ ከጎረቤቶቿ ጋር የሚያስተሳስራት 13 ነጥቦች

የቀጣናውን ሀብት ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# ሻሻ - የነዋሪዎች የደኅንነት ስጋት

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

*ዜና ሐተታ*

ድርጊቱ ለነዋሪው የደኅንነት ስጋትና ፈተና ሆኗል፡፡ የችግሩ ገፈት ቀማሽ የሆኑ ግለሰቦች ለማኅበራዊ፣ ሥነ-ልቦናዊ፣ አካላዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና ይወድቃሉ ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በጠራራ ፀሐይ ንብረቴን ተቀማሁ እያለ የሚጮኸው ተበራክቷል፡፡ በከተማው የሚፈጸመው ይህ እኩይ ተግባር ለነዋሪዎቹ ቀውስና ፈተናን እየደቀነ ቀጥሏል፡፡

ወጣት ገነት ግርማ (ስሟ የተቀየረ) የዚህ ወንጀል ገፈት ቀማሽ ነች። ከመገናኛ ወደ ሃያ ሁለት ለመሄድ ነው ከቤቷ የወጣችው። ከዚያም መደበኛ ሥራውን እየሠራ ወደሚመስለው ታክሲ ገባች፡፡ ጉዞ ከጀመረች

ሻሻ - የነዋሪዎች ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# ከንቲባ አዳነች አቤቤ ለልማት ተነሺዎች የመኖሪያ ቤት ሕንፃ ግንባታ አስጀመሩ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ለልማት ተነሺዎች የሚሆን የመኖሪያ ቤት ሕንፃ ግንባታ አስጀመሩ።

ከንቲባ አዳነች በልደታ ክፍለ ከተማ የሚገነባውን

ከንቲባ አዳነች አቤቤ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል






ወይዘሮ ሙፈሪያት ካሚል

# በስድስት ወራት ከ181 ሺህ በላይ የውጭ ሀገር የሥራ ዕድል ተፈጥሯል

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- በስድስት ወራት በውጭ ሀገር 181 ሺህ 483 የሥራ ዕድል መፍጠር መቻሉን የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ወይዘሮ ሙፈሪያት ካሚል ገለጹ፡፡

ሚኒስትሯ ወይዘሮ ሙፈሪያት ይህንን የተናገሩት ሰሞኑን በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሰው ሀብት ልማት፣ ሥራ ስምሪትና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የተቋማቸውን የስድስት ወራት የሥራ አፈፃፀም በገመገመበት ወቅት ነው።

በሥራ ዕድል ፈጠራ በውጭ አገር በስድስት ወራት 250 ሺህ ሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ 181 ሺህ 483 መሳካቱን፣ በሀገር ውስጥ ደግሞ ሁለት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ሥራ ለመፍጠር ታቅዶ አንድ ነጥብ ሦስት ሚሊዮን መፍጠር መቻሉን በሪፖርታቸው አመልክተዋል፡፡

ምሩቃን ከቅጥር ይልቅ የሥራ ፈጠራ መንገዶችን እንዲከተሉ ተቋማቸው እንደሚያበረታታም ነው ወይዘሮ ሙፈሪያት የተናገሩት፡፡

የውጭ ሥራ ስምሪቱ ዜጎች መብታቸው ተጠብቆ፣ የባንክ ለባንክ ሥርዓት ተፈጥሮ እና ተመልሰው በልማት እንዲሳተፉ በሀገር ኢኮኖሚ ላይም አስተዋፅዖ ማድረግ እንዲችሉ አስተማማኝ ሥርዓት የተፈጠረበት መሆኑንም ነው የገለጹት፡፡

ባለፉት ስምንት ወራት ሕጋዊ የምዝገባ ሥርዓቱን ተከትለው የሄዱ ዜጎች ስላሉበት ሁኔታ ሙሉ መረጃ ለማግኘት እንደተቻለ አንስተዋል፡፡ 700 ሺህ በላይ ዜጎች ለውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት መመዝገባቸውንም ጠቁመዋል፡፡

የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪትን ለማስፋት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በቀጣይ ከሦስት አዳዲስ መዳረሻ ሀገራት ጋር ስምምነት ለመፈረም ሂደት ላይ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

የሥራ ላይ አደጋ ምርመራ ሥራ በ312 ተቋማት ላይ መከናወኑን ጠቁመው፤ የደኅንነት መጠበቂያ እቃዎችን በብቃት አለማቅረብ እና አንዳንድ ተቋማት ደግሞ ሠራተኞች የቀረቡትን የደህንነት መጠበቂያ ግብዓቶችን ባግባቡ አለመጠቀም በምልከታው መታዘብ እንደተቻለም ነው የገለጹት፡፡

የኢትዮጵያ የገበያ መረጃ ሥርዓትን በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ ሥራው ተጠናክሮ መቀጠሉን ተናግረው፤ ስድስት ሺህ የሚሆኑ በቤት ውስጥ የተሠማሩ ዜጎች ተመዝግበዋል ብለዋል፡፡

ምዝገባው በቤት ውስጥ ሥራ ለተሠማሩና ለቀጣሪዎች ዋስትና የሚሰጥ ሲሆን በሁለቱም ተዋናዮች መካከል ሠላማዊ የሥራ ግንኙነት የሚፈጥር መሆኑንም አመልክተዋል፡፡

# ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሔ ለመስጠት ቁልፍ ሚና እየተጫወተች ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**



ፎቶ - በረሀኑ ታደሰ

ፓትርክ ሳኩሬ እና ባለቤታቸው ካርመን ካስትሮ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሔ ለመስጠት ቁልፍ ሚና የምትጫወት ሀገር መሆኗን በኢትዮጵያ የካናዳ ኤምባሲ የፖለቲካ እና የሕዝብ ጉዳዮች አማካሪ ፓትሪክ ላኩሬ ገለጹ፡፡

በኢትዮጵያ የካናዳ ኤምባሲ የፖለቲካ እና የሕዝብ ጉዳዮች አማካሪ ፓትርክ ላኩሬ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ የቀጣናዊ ውሕደትን ለማፋጠንና ሠላም ለማስፈን ለአፍሪካ ተግዳሮቶች አፍሪካዊ መፍትሔ መስጠት አለበት በሚል እሳቤ ላይ እየሠራች መሆኑ ለአፍሪካ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሔ ለመስጠት ኢትዮጵያ ቁልፍ ሚና መጫወት የምትችል ሀገር እንደሆነች ማሳያ ነው፡፡

እንደ ፓትርክ ላኩሬ ገለጻ፤ የሥነ ሕዝብ አወቃቀር ችግሮች፣ የሕዝብ ቁጥር መጨመር፣ በአህጉሪቱ የድሀ ኅብረተሰብ ክፍሎች በብዛት መገኘት፤ እንዲሁም ግጭቶች እያደጉ መምጣታቸውና በብዙ ሀገራት መፈንቅለ መንግሥቶችም መካሄዳቸው የአፍሪካ ፈተናዎች ናቸው።

አትዮጵያ የጀመረችውን እሳቤ በማጽናት በአህጉሪቱ ሠላም እንዲሰፍን ሁሉም አፍሪካውያን የተቀናጁና የጋራ መፍትሔዎችን በአንድነት በማሰባሰብ፤ ብልጽግናን በማስፈንና የበለጠ ዲሞክራሲን በማስረጽ የተሻሉ የጤና፣ የትምህርትና የተለያዩ ተቋማትን መገንባት አስፈላጊ ነው፤ ለዚህም ኢትዮጵያ ትልቅ ሚና መጫወት ትችላለች ብዬ አስባለሁ ብለዋል።

ካናዳ ለእሳቤው መሳካት የምትችለውን ያህል ድጋፍ እንደምታደርግ ጠቁመው፣ ለአፍሪካ ችግሮች መፍትሔዎች ከአፍሪካ መምጣት አለባቸው ብለን እናስባለን ነው ያሉት።

አክለውም አሁን ባለው ሁኔታ ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲው መስክ በጥሩ ሁኔታ እየሠራች በመሆኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላት ተቀባይነትም እየጨመረ መጥቷል። ለዚህም በቅርቡ በዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ መስኮች ላይ ተፅዕኖው እየጨመረ የመጣውን የብሪክስ ቡድን መቀላቀሏ ማሳያ መሆኑን አንስተዋል፡፡

“ዲፕሎማሲ የዕለት ተዕለት ሥራዬ ነው፤ ሆኖም ግን እንደዚህ በሚያምር መልኩ ዲፕሎማሲን መመልከት በሙያው ላይ ላለ ሰው በጣም አስደሳች ነው” ያሉት አማካሪው፤ በውጭ ጉዳይ ተዘጋጅቶ የነበረው ዓውደ ርዕይ የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ከክርስቶስ ልደት በፊት ንግሥት ሳባ ወደ እስራኤል ባደረገችው ጉዞ የጀመረና በዓለም ላይ ካሉት ጥንታዊ ዲፕሎማሲዎች አንዱ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው ብለዋል።

በዓውደ ርዕዩ እንደቀረበው የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ከቡና ጀምሮ የአየር መንገድ፣ የባሕል፣ የስፖርትና ሌሎች የዲፕሎማሲ ቅርጾችንም ያካተተ ነው፤ ይህን ሁሉ በአንድ ላይ በማየቴ እጅጉን ተደስቻለሁ ነው ያሉት።

"ካናዳና ኢትዮጵያ የቆየ የዲፕሎማሲ ታሪክ አላቸው። ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት የጀመሩት እ.አ.አ በ1965 ነው" ያሉት አማካሪው፤ የሁለቱን ሀገራት ግንኙነት ለማሳደግና ሁለቱም ወገኖች የበለጠ ጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ መሥራታቸውን እንደሚቀጥሉ ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ እጅግ በጣም ተግባቢ እና እንግዳ ተቀባይ መሆኑ የሀገራቱን ግንኙነት በማሳደግ በጋራ ለመሥራት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥርም አንስተዋል።

ባለቤታቸው ካርመን ካስትሮ በበኩላቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሌም ከፊቱ ፈገግታ የማይለየውና የብዝኃ ባሕል ባለቤት መሆኑ እንደሚያስደምማቸው ገልጸው፤ የኢትዮጵያን የበለጸገ ታሪክ ለማወቅ እድል በማግኘቴ እጅግ ደስተኛ ነኝ ብለዋል።

በጅግጅጋ ከተማ በተከበረው የብሔር ብሔረሰቦች በዓል ላይ በመሳተፍ የኢትዮጵያውያንን ሁሉንም የባሕል መገለጫዎች ማየታቸውን የሚናገሩት ካርመን፤ የኢትዮጵያን በብዝኃነት ያሸበረቀ ባሕልና ማንነት መመልከት አስደናቂ መሆኑን ገልጸዋል።

# በመዲናዋ ከ48 ሺህ በላይ ለሆኑ ሴቶች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል

**አመለወርቅ ከበደ**



ወይዘሮ ወይንሸት ዘሪሁን

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ በ2016 በጀት ዓመት ስድስት ወራት ከ48 ሺህ በላይ ለሆኑ ሴቶች የሥራ ዕድል መፈጠሩን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ ገለጸ፡፡ በ98 ጤና ጣቢያዎች በሴቶች ጤና ላይ ያተኮሩ ምርመራዎች እየተካሄዱ ነው።

በዓለም ለ113ኛ ግዜ በኢትዮጵያ ለ48 ጊዜ ‹‹ሴቶችን እናብቃ፤ ልማትና ሠላምን እናረጋግጥ›› በሚል መሪ ቃል የሚከበረውን የሴቶች ቀንን አስመልክቶ ቢሮው ባለፈው ሳምንት መግለጫ ሰጥቷል፡፡

የቢሮው ኃላፊ ወይዘሮ ወይንሸት ዘሪሁን በወቅቱ እንደተናገሩት፤ በ2016 ዓ.ም በስድስት ወራት ከ48 ሺህ በላይ ሴቶች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል።

በሁለተኛው ግማሽ ዓመት የመጀመሪያው ሦስት ወራት ለ36 ሺህ ሴቶች የሥራ ዕድል ለመፍጠር እየተሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ ቢሮው በከተማዋ የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ ትኩረት ማድረጉን አስረድተዋል።

ለሴቶች በቂ ሥልጠና በመስጠት በተለያዩ ሆቴሎች፣ ኢንዱስትሪዎችና የተለያዩ ተቋማት እንዲቀጠሩ መደረጉን አመላክተዋል፤ በተጨማሪም ተደራጅተው የብድር ዕድል የተመቻቸላቸው ሴቶች እንዳሉ ተናግረዋል።

የሴቶችን አመለካከት ለመቀየር በሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ ያተኮረ ሥልጠና መሰጠቱን ገልጸው፤ ሥልጠናውም ከ20 ሺህ በላይ ሴቶች ለሆኑ ሴቶች ተደራሽ መሆኑን አስታውቀዋል።

ምንም ገቢ የሌላቸው ነገር ግን ተነሳሽነት ያላቸው ለአንድ ሺህ 51 ሴቶች በሥራ ፈጠራና ቁጠባ ላይ ያተኮረ ሥልጠና ተሰጥቷል ብለዋል፡፡

በየካቲት ወር 2016 ዓ.ም ለሴቶች የሥራ ማስጀመሪያ የሚውል 10 ሚሊዮን 510 ሺህ ብር በጀት በመመደብ እየተሠራ ይገኛል ሲሉ ገልጸዋል።

በተጨማሪም ለጤናማ እናትነት ሴቶች ከእርግዝናቸው ጀምሮ የጤና ክትትል እንዲያደርጉ፤ በጤና ተቋማት እንዲወልዱ ፤ የማሕፀን በርና የጡት ካንሰር ቅድመ ምርመራ እንዲያደረጉ ከጤና ቢሮው ጋር በመሆን በ98 ጤና ጣቢያዎች ምርመራ እየተደረገ ይገኛል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

በጤና ዙሪያ ለ20 ሺህ ሴቶች የግንዛቤ ማስጨበጫ መሰጠቱን የተናገሩት ወይዘሮ ወይንሸት፤ ግንዛቤ ከተፈጠረላቸው ሴቶች ሦስት ሺህ እናቶች የማሕጸን በርና የጡት ካንሰር ምርመራ አድርገዋል ሲሉ ገልጸዋል።

በተያዘው በጀት ዓመት ቁጥራቸው ከ10 ሺህ በላይ የሚሆን የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ያሉባቸው ሕጻናት፣ ነፍሰጡር እና ለሚያጠቡ እናቶች የአልሚ ምግብ ተጠቃሚ ለማድረግ በየዓመቱ 259 ሚሊዮን ብር በመመደብ እየተሠራ ይገኛል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በሌላ በኩል ወይዘሮ ወይንሸት እንዳሉት፤ የሴቶች ቀንን ምክንያት በማድረግ የእናቶችን ሞት ለመቀነስ በተለያዩ ክፍለ ከተማዎች የደም ልገሳ እየተካሄደ ይገኛል።

በዚህም አንድ ሺህ ዩኒት ደም ለመሰብሰብ የታቀደ ሲሆን ባለፉት ጊዜያት የተሰበሰበው የደም መጠን 830 ዩኒት ነው። በተጨማሪም በቀጣይ እሁድ ቀኑን ምክንያት በማድረግ የእሩጫ ውድድር ይካሄዳል። አምስት ሺህ ሴቶች ይሳተፋሉ ሲሉ ገልፀዋል።

የሴቶች ቀንን በማስመልከት በሚደረገው የደም ልገሳ የከተማው ነዋሪዎች እንዲሳተፉ እና በቀጣይ እሁድ በሚደረገው የሩጫ ውድድር የከተማዋ ሴቶች ተሳትፈው እህትማማችነትን እንዲያጠናክሩ ጥሪ አቅርበዋል።



አቶ ዘውዱ ሳሙኤል

# በዘጠነኛው የከተሞች ፎረም ዘመናዊ ከተሞችን ከመገንባት አንጻር በቂ የልምድ ልውውጥ ተደርጓል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በወላይታ ዞን ሶዶ ከተማ የተከበረው ዘጠነኛው የከተሞች ፎረም ከተሞችን ከማዘመን አንጻር ሰፊ የልምድ ልውውጥ የተደረገበት መሆኑን የዞኑ ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ አስታወቀ፡፡

የመምሪያው ኃላፊ አቶ ዘውዱ ሳሙኤል ለኢፕድ እንደገለጹት፤ “የዘመኑ ከተሞች ለኢትዮጵያ ብልጽግና” በሚል መሪ ሃሳብ የተከበረው ዘጠነኛው የከተሞች ሳምንት ለኑሮ ምቹ የሆኑ ከተሞችን ለመገንባትና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚረዱ የልምድ ልውውጦች ተካሂደውበታል።

የከተሞች ፎረም ሲዘጋጅ ኅብረተሰቡን በማሳተፍ በከተማ አመራሮች መካከል ልምዶችን ለመለዋወጥ፣ ትብብርን ለማጠናከርና ለማኅበራዊ ችግሮች መፍትሔ የሚያመጡ አቅጣጫዎችን ለማስቀመጥ ታልሞ እንደመሆኑ ዓላማውን አሳክቷል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

በዝግጅቱ ላይ ከ125 በላይ ከተሞች ተሳትፈዋል ያሉት ኃላፊው፤ ትብብርን ከማጠናከር አንጻር ከተለያዩ ከተሞች ጋር በጋራ ለመሥራት ስምምነት መደረጉንና ከፎረሙ ጎን ለጎን የፓናል ውይይቶች መካሄዳቸውን አስታውሰዋል።

መርሐ ግብሩን የተሳካ ለማድረግ ከ25 ሄክታር በላይ መሬት ተዘጋጅቶ በቦታው የመብራት፣ የተለያዩ የኢትዮ-ቴሌኮም አገልግሎቶች እንዲሟሉ መደረጉን ጠቁመው፤ አካባቢውን የማሳመር ሥራ ተሠርቷል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

በሌላ በኩል ዝግጅቱ የኢኮኖሚ መነቃቃት መፈጠሩን አስታውቀው፤ በዝግጅቱ የተሳተፉ አዳዲስ ድርጅቶች በሶዶ ከተማ ለማልማት ፍላጎቶች ማሳየታቸውንና በከተማው እየሠሩ የሚገኙ ድርጅቶችና ባለሀብቶች በገቢ ደረጃ መነቃቃት እንደተፈጠረላቸው ገልጸዋል፡፡

አቶ ዘውዱ እንደተናገሩት፤ የወላይታ ከተማ አስተዳደር ከተማን ከማዘመን አንጻር ከወረቀት ነፃ የሆነ ሥራ ለመሥራት፣ የመሬት ምዝገባን በዘመናዊ መንገድ ለመከወን የስማርት ሲቲ መርሕን ተከትሎ እየሠራ ነው፡፡

እንደ ኃላፊው ገለጻ፤ በመርሐ ግብሩ አማካኝነት የሶዶ ከተማና ሌሎች በዞኑ የሚገኙ ከተሞች አመራሮች ከአዲስ አበባ፣ ከአዳማና ከሌሎች ከተሞች አመራርና ባለሙያዎች ጋር የልምድ ልውውጥ አካሂደዋል።

ከፀጥታ አንጻርም ዝግጅቱን ለመታደም የሚመጡ ተሳታፊዎች ያለምንም የፀጥታ ችግር እንዲያከብሩ ለሠላምና ፀጥታ ኅብረተሰቡን ባለቤት ለማድረግ ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር ወይይት ተካሄዷል ያሉት ኃላፊው፤ በመሆኑም ዝግጅቱ ያለምንም የጸጥታ ችግር እንደተከበረ ተናግረዋል፡፡

ለዝግጅቱ የጊዜ እጥረት እንደነበር እና ይህም እንደክፍተት የተወሰደ ሲሆን፤ በቀጣይ የከተሞች ፎረም የሚካሄድባቸው ከተሞች ላይ ቀደም ብሎ ዝግጅት መጀመር እንዳለበት አመላክተዋል።

ከየካቲት 9-15 ቀን 2016 ዓ.ም በወላይታ ሶዶ ከተማ በተከበረው የከተሞች ፎረም ዝግጅት ላይ ለተሳተፉ አካላት ኃላፊው ምስጋና አቅርበዋል፡፡

# ለጢያ ትክል ድንጋይ ማስፋፊያ ፕሮጀክት የሚውል 28 ሚሊዮን ብር ተሰበሰበ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**



አዲስ አበባ፡- ከመደመር ትውልድ መጽሐፍ ሽያጭ ለጢያ ትክል ድንጋይ ዓለም አቀፍ መካነ ቅርስ ማስፋፊያ ፕሮጀክት የሚውል 28 ሚሊዮን ብር መሰብሰቡን የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ፡፡ የማስፋፊያ ፕሮጀክቱ ሙሉ ዲዛይን ተሠርቶ መጠናቀቁን ቢሮው ጨምሮ ገልጿል።

የክልሉ ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ አቶ ሳሙኤል መንገሻ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ ከመደመር ትውልድ መጽሐፍ ሽያጭ ለጢያ ትክል ድንጋይ ማስፋፊያ ፕሮጀክት የሚውል 28 ሚሊዮን ብር ተሰብስቧል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በክልሉ ከመደመር መጽሐፍ ሽያጭ ለቅርሱ ማስፋፊያ መስጠታቸውን ያስታወሱት አቶ ሳሙኤል፤ በዚህ መሠረትም በተደረገ የገቢ ማሰባሰቢያ መድረክ ከ240 ሚሊዮን ብር በላይ ቃል ተገብቶ እስካሁን 28 ሚሊዮን ብሩ ተሰብስቧል ብለዋል፡፡

ማስፋፊያ ፕሮጀክቱ የአካባቢው ኢኮ ቱሪዝምና የሥራ ዕድል ፈጠራን ሊያስፋፉ የሚችሉ የሆቴል ግንባታዎች፣ የማኅበረሰብ ሎጆች እንዲሁም ዘመናዊ ሎጆች የሚያካትት መሆኑን አቶ ሳሙኤል ጠቁመዋል።

አቶ ሳሙኤል አክለውም፤ ዓለም አቀፍ መካነ ቅርሱ ያለበት የምሥራቅ ጉራጌ ዞን በአዲስ ከመዋቀሩ ጋር ተያይዞ በተፈለገው ጊዜ ብሩን ለመሰብሰብ አዳጋች ሆኗል ያሉ ሲሆን፤ የማስፋፊያ ፕሮጀክቱ በተፈለገው ጊዜ ጀምሮ ለማጠናቀቅ ተጠሪነቱ ለክልሉ የሆነ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት ተቋቁሞ እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

እንደ አቶ ሳሙኤል ገለጻ፤ በክልሉ በርካታ የቱሪስት መዳረሻ ስፍራዎች እየለሙ ነው፡፡ ክልሉ በቱሪዝም ዘርፍ ሰፋፊ ሀብት ቢኖሩትም ባለፉት ጊዜያት ለዘርፉ ብዙ ትኩረት ሳይሰጠው እንደቆየ አንስተዋል፡፡

የማስፋፊያ ፕሮጀክት ዲዛይን ተጠናቆ ጨረታ የማውጣት ሂደት ላይ ይገኛል ያሉት አቶ ሳሙኤል፤ በውስጡ ሰባት ፕሮጀክት እንደሚይዝ አመላክተዋል።

አቶ ሳሙኤል እንዳሉት፤ ቃል የተገባው ገንዘብ እስከ መጋቢት አጋማሽ ድረስ ቢያንስ 50 በመቶ በላይ የሚሆነው እንዲጠናቀቅ እቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው፡፡

ክልሉ በአዲስ ከተዋቀረ በኋላ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ቱሪስት ፍሰት ቁጥር ከፍ በማለቱ ከቱሪዝም የሚገኘው ገቢ እየጨመረ መምጣቱንም ነው አቶ ሳሙኤል የተናገሩት፡፡

በበጀት ዓመቱ በመጀመሪያዎቹ አምስት ወራት ከ50 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ መገኘቱን አቶ ሳሙኤል አስታውሰዋል፡፡

አካባቢው ከሀገሪቱ ዋና ከተማ በቅርብ ርቀት የሚገኝ በመሆኑና ሙሉ በሙሉ ሠላም ያለበት በመሆኑ በቱሪዝም ዘርፉ አመርቂ ውጤት ለማግኘት የተሻለ አማራጮች እንዳሉት አስገንዝበዋል፡፡

# በክልሉ በ78 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የተፋሰስ ልማት ሥራ ተሠርቷል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**



አቶ ዑስማን ሱሩር

አዲስ አበባ፡- በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በሕዝብ ንቅናቄ በአንድ ሺህ 300 ንዑስ ተፋሰሶች 78 ሺህ ሄክታር መሬት በተፋሰስ ሥራ መልማቱን የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ፡፡ በተፋሰስ ልማቱ ከአንድ ነጥብ 89 ሚሊዮን በላይ ሰዎች መሳተፋቸውን ቢሮው ጨምሮ ገልጿል፡፡

በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የክልሉ የገጠር ክላስተር አስተባባሪና የግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ዑስማን ሱሩር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በተያዘው በጀት ዓመት በሕዝብ ንቅናቄ በክልሉ በ78 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የተፋሰስ ልማት ሥራ ተሠርቷል፡፡

በክልሉ በሁሉም ዞኖችና ሦስት ልዩ ወረዳዎች ላይ የበጋ ወቅት የተቀናጁ የተፋሰስ ሥራዎች ተሠርተዋል ያሉት አቶ ዑስማን፤ በልማት ሥራው አንድ ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ሰዎች በቀጥታ ለማሳተፍ ታቅዶ እስካሁን ከአንድ ነጥብ 89 ሚሊዮን በላይ ሰዎች መሳተፋቸውን ጠቁመዋል፡፡

በተጨማሪም 156 ሺህ ሰዎች አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች በማቅረብና በማስተባበር ሥራ መሳተፋቸውን ነው ያስታወቁት፡፡

አቶ ዑስማን አክለውም፤ የተፋሰስ ልማት ንቅናቄው እስከ የካቲት 30 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ይቆያል ያሉ ሲሆን፤ 147 ሺህ ሄክታር መሬት በተፋሰስ ልማት ለማልማት ታቅዶ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

ከዚህ በፊት በተሠሩ ሥራዎች በርካታ የተራቆቱ መሬቶች አገግመው የመስኖ አቅሞች ማሳደግ መቻላቸውን ጠቁመው፤ በርካታ ወንዞችና ሐይቆች ከደለል ሙላት መከላከል ተችሏል ብለዋል፡፡

ያገገሙት መሬቶች እንዲሁም ለአካባቢው ማኅበረሰብ የሥራ ዕድልና የገቢ ምንጭ መሆን መቻላቸውን አቶ ዑስማን ተናግረዋል፡፡

የተቀናጀ የተፋሰስ ሥራ በተሠራባቸው አካባቢዎች የተተከሉ የፍራፍሬ ዛፎች የተሻለ ምርት መስጠት ጀምረዋልም ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ዑስማን ገለጻ፤ በክልሉ ከተፋሰስ ልማቱ ጎን ለጎን የበልግ የልማት ሥራዎች ልዩ ትኩረት በመስጠት እየተሠራ ነው፡፡ ከዚህ በፊት ለምርትና ምርታማነት ማነቆ የሆኑ ችግሮች በመለየት መፍታት ተችሏል፡፡

በተጨማሪም የግብርናው ዘርፍ በቴክኖሎጂ የተደገፈ እንዲሆን ተደርጎ የበልግ እርሻው በንቅናቄ እንዲመራ መደረጉን ገልጸዋል፡፡

በተለይ በልግን ቀድመው የሚጀምሩ አካባቢዎች ላይ የግብዓት አቅርቦት ችግር እንዳይከሰት መሠራቱን አያይዘው አመላክተዋል፡፡

የተፋሰስ ልማት ለአጠቃላይ የግብርና ምርትና ምርታማነት ከማሳደግ እንዲሁም ከኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ጎን ለጎን አካባቢያዊ የተስተካከለ ሥነ-ምሕዳር ከመፍጠር አኳያ ሰፊ ጠቀሜታ እንዳለው ያስታወሱት አቶ ዑስማን፤ በቀጣይም የተሠሩ ሥራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ ብለዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የዓድዋን ድል ታላቅነት በሰላምና በልማት ደግመን እናግዝፈው!

የዓድዋ ድል ከዓለም ታላላቅ የታሪክ ክስተቶች መካከል አንዱ ሲሆን፤ ለኢትዮጵያውያን የኩራትና የጀግንነት ምልክት፤ ለመላው ጥቁርና ጭቁኖች ደግሞ የነጻነትና እኩልነት ብርሃን ነው፡፡ ምክንያቱም ከዓድዋ ጦርነት በፊት በነጮችና ጥቁሮች መካከል የነበረው ተፈጥሯዊ ግንኙነት የተዛባ ነበር። ነጮቹ ራሳቸውን እንደ ገዢ ሲቆጠሩ፣ ጥቁሮቹን ደግሞ እንደ ተገዢ ሕዝብ ይቆጥሩት ነበር።

በዚህም ጥቁሮቹ ራሳቸውን የማስተዳደር አቅምና ችሎታ እንደሌላቸው፤ ይልቁንም ነጮች ጥቁሮችን የመግዛት ሙሉ መብት እንዳላቸው ያምኑ ነበር፡፡ በተጨማሪም ጥቁሮች ባህልና ታሪክ አልባ፤ እንዲሁም በተፈጥሯቸው ያልተሟሉ የሰው ዘሮች እንደሆኑ ተደርጎ ይነገር ነበር። እናም የዓድዋ ድል በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ይህን ሁሉ ቀይሯል፡፡

በአውሮፓውያን በኩል፣ ነጮች ይከተሉት የነበረው የተዛባ ትርክት "የነጭ ዘር የበላይነት" መንኮታኮትና እርቃኑን መቅረት የጀመረው በዓድዋ ድል ምክንያት ነው። ከዚህ ድል በኋላ ኢምፔሪያሊስቶች አፍሪካ ላይ የነበራቸው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጥቅሞች ተናግተዋል። የጭቆና መረባቸውም አቅም አጥቷል፡፡

ይህ ሁሉ ድል የተገኘው ጀግኖች ኢትዮጵያውያን አጥንታቸውን ከስክሰው፤ ደማቸውን አፍሰውና ሕይወታቸውን ገብረው በከፈሉት መስዋዕትነት ነው፡፡ ድሉ ግን ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ጥቁር ሕዝቦች እኩልነት የተከፈለ የደም ዋጋ ነው። ለዚህም ነው የዓድዋ ድል በዓል በሰው ልጆች ነፃነትና እኩልነት የሚያምን ማንኛውም የሰው ዘር ሊያከብረውና ሊዘክረው የሚገባ ክስተት ሆኖ የዘለቀው፡፡

ኢትዮጵያ ቀደምትና ታሪካዊት ሀገር፤ ሕዝቧም የዚህ ታላቅ ድል ባለቤት ነው፡፡ ይህ ጀግና ሕዝብ የብሄር፤ የሃይማኖት፣ የጾታ እና ሌሎች ሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ ልዩነቶች ሳይበግሩት በአንድነት በመትመም ቅኝ ገዢዎችን አሳፍሮ መልሷል፡፡ ለሉዓላዊነቱና ለነጻነቱ እረፍት የማያውቀው ይህ ሕዝብ ታዲያ፤ ሀገሩ የቅኝ ግዛት ጥማት ባለው ኃይል ልትወረር መሆኑን በሰማበት ቅጽበት ቀፎ እንደተነካበት ንብ ከአራቱም ማዕዘናት በአንድነት ተሰባስቦ ወረራውን ቀልብሷል፤ ሀገሩን ከወራሪ ታድጎም የድል ታሪኩን ጽፏል፡፡ በዚህም ለመላው ጥቁር ሕዝቦች የይቻላልን ሰብዕና አጎናጽፎ ለነጻነታቸው እንዲታገሉ ዓርአያ ሆኗቸዋል፡፡

የዚህ ባለታሪክ ትውልድ ልጆች የሆንነው እኛ የዛሬው ትውልዶችም፤ ከቀደምቶቻችን ተግባር ልንቀስመው ከሚገባው ዘርፈ ብዙ ትምህርት ባለፈ፤ ለውለታቸው ልንከፍል የሚገባን፣ ሀገርና ሕዝብን ከዛሬ በማሻገር ሂደት ውስጥ ልንወጣ የሚገባን ብዙ የቤት ሥራ አለ፡፡ ለምሳሌ፣ ለሀገር ሉዓላዊነትና ለግዛት አንድነት የሕይወት መስዋዕትነት የከፈሉ ጀግኖች ውለታ ከሚመለስባቸው ጉዳዮች አንዱ፤ የኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያውያንን ሰላም ማስጠበቅ፣ ልማትን እውን ማድረግ በመቻል ውስጥ ነው፡፡

ለዚህ ደግሞ ከእኛ የጦር ሜዳ አርበኛ መሆን አይደለም የሚጠበቅብን፤ የሰላም እና የልማት መስኩ አርበኛ መሆን መሆን እንጂ፡፡ በተለይም ዛሬ ላይ በተለያዩ ምክንያቶች በሰላም ችግር እየተፈተነች ላለች ሀገራችን እና ሰላምን ለሚሻው ሕዝባችን የሰላም አምባሳደር በመሆን በመሥራት የአባቶቻችንን መስዋዕትነት ለማጽናት የበኩላችንን ጥረት ልናደርግ ይገባል፡፡

ምክንያቱም እኛ ኢትዮጵያውያን ላለፉት ሃምሳ እና ስድሳ ዓመታት ከአንድነት ይልቅ የልዩነት ጉዳዮቻችንን እያጎላን ሕብረታችንን ለማላላት ጥረናል፡፡ በዚህም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ሰላማችንን በገዛ ራሳችን እያጠፋን መጥተናል፡፡ በመሆኑም ዛሬ ላይ የግጭት፣ የጦርነት፣ ያለመግባባት ታሪካችን ተዘግቶ በጋራ ታሪኮቻችን ላይ የምንግባባ፤ ለጋራ ሀገራችን የምንተጋ፤ ለልጆቻችንም የበለጸገች ኢትዮጵያን ለማውረስ የጋራ እሳቤ የምናኖር የለውጥ ትውልድ መሆን ይገባናል፡፡

በአባቶቻችንና እናቶቻችን ተጋድሎ ያገኘነው ኩራትና ነጻነታችን ሙሉ እንዲሆን ኢትዮጵያን በሁሉም መስክ ማበልጸግ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ ደግሞ የተጀመሩ የብልጽግና አውታሮችን ማጠናቀቅ፤ አዳዲስ የትውልዱን ታሪክ የሚያደምቁ ሥራዎችን መጀመር ይጠይቃል፡፡ ለአብነት፣ ይህ ትውልድ ታላቁን የዓባይ ግድብ ሰርቶ እያገባደደ ነው፡ ፡ ይህን የሀገር ኩራት የሆነ ግድብ አጠናቆ ለሀገር ብሎም ለአፍሪካ ብርሃን ማጎናጸፍ የዚህ ትውልድ አንዱ አደራ ነው፡፡

በግብርና ልማት በተለይም በስንዴ የተገኘውን አኩሪ እንቅስቃሴ ዘላቂ ማድረግና ከኢትዮጵያም አልፎ አፍሪካን መመገብ ሌላው የዚህ ትውልድ ዐሻራ ሊሆን ይገባል፡፡ አረንጓዴ ዐሻራ በማኖር ረገድ ኢትዮጵያውያን ባለፉት አምስት ዓመታት አዲስ ታሪክ በመጻፍ ላይ ይገኛሉ፡፡

ይህ አኩሪ እንቅስቃሴ የኢትዮጵያን ልማትና ዕድገት የማይወዱ አካላት ሊያጣጥሉት ቢሞክሩም፤ ተግባሩ የሚደበቅ አይደለምና ኢትዮጵያ በተሳተፈችባቸው መድረኮች ሁሉ በውጤታማነቱ እየተወሳ ይገኛል፡፡ ስለዚህም ትውልዱ ይህንን አንጻባራቂ እንቅስቃሴ ከዳር ማድረስና ኢትዮጵያን ብሎም አፍሪካን አረንጓዴ ማልበስ ቀጣይ የቤት ሥራው ሊሆን ይገባል፡፡

በአጠቃላይ ኢትዮጵያውያን ቀደም ሲል በዓድዋም ሆነ በሌሎች የጦር አውድማዎች የሀገርን ዳር ድንበር አላስደፍርም በማለት ደማቸውን በማፍሰስ፤ አጥንታቸውን በመከስከስ ውድ ሕይወታቸውን መስዋዕት እያደረጉ ሀገርን በነጻነት አጽንተው ኖረዋል፡፡ የአሁኑ ትውልድም የሀገሩን ዳርድንበርና ሉዓላዊነት ከመጠበቅ ጎን ለጎን በሰላም እና በልማቱም መስክ ሀገሪቱን ወደ ፊት ሊያራምዱ የሚያስችሉ ተግባራትን በመፈጸም ነጻነቷን ምሉዕ በማድረግ የቀደምት አባቶችን ፈለግ ሊከተል፤ እንደ ዓድዋም የሚዘከር የራሱን ታሪክ ሊያኖር ይገባል፡፡


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ታላቁ ዓድዋ ከከያኒዋ አንደበት

ስብሥራት

የዓድዋን ጦርነትና ድል በጥሞና ስቃኝ፣ የእንባ ጤዛና የድል ዜማ ማዶ ለማዶ ሆነው በአእምሮዬ ጓዳ ድቅን ይሉብኛል። በተለይም የዓድዋን መዝሙር በእጅጋየሁ ሽባባው ሙዚቃ ውስጥ ሳደምጥ ልክ እንደ ሙዚቃው፤ በኩራት፣ በክብር፣ በደስታ፣ በፍቅር፣ ደግሞም በኀዘን እኖራለሁ።

ይህ ድብልቅልቅ ስሜት፣ ረቂቅ ትውስታ ሁለት ገጽታ ያለው የሁሌ ትዝታ፣ መዝሙርና ሙሾ በአንድ ሰዓት በአንድ ሀሳብ በውስጤ ይመላለሳሉ። በጦርነቱ ዕለት፤ ከዚያ አስደናቂ ድል በኋላ በዐፄ ምኒሊክ፣ በራስ መኮንንና ሌሎችም ጀግኖች ፊትና ልብ ላይ የሚንቀዋለል ስሜት ዛሬ ላይ የሆነ ያህል እንዲታየን ሆኗል።

ከዚህ አንፀባራቂ ድል በኋላ የወደቁት እነ ፊታውራሪ ገበየሁ (አባ ጎራውን) የመሳሰሉ ጀግኖች ሞት ለጓዶቻቸው ሕመም ነበር። ሰው ከፍሎ፣ ውድን ሰጥቶ ሌላ ውድ ነገር መቀበል ቀላል ያልነበረ መሆኑንም በእንባና ሳቅ ድብልቅ ስሜት እንድናይ ሆነናል።

ጀግኖቻችን የዓለም ዕብሪተኛ በስላቅ ምላሱን አውጥቶ እንዳያላግጥብን፣ የተሳለልንን ቢላዋ ነጥቀው፣ ቀንበሩን ከጫንቃችን የሰበሩት በራሳቸው ደም ነው፤ የድል ዜና ያሰሙን፣ ገድሉን የፈጸሙትና በታሪካችን ላይ ዘውድ የደፉት ከጠላት ጋር ተናንቀው ደምና ላብ ከፍለው ነው። ዛሬ ሲታሰቡን የማያረጁና በታሪካችን ገጾች የማይደበዝዙ ዝርግፍ ጌጦቻችን ሆነው ነው፤ ለዚህም ነው ከልብ የማይጠፋ ክብር ነፍስያችን ውስጥ ያኖሩት።

የድል ቦታዋ ዓድዋ ሰንሰለታማ ሰፈር አይደለችም፤ በትንሽ መንደርም አትመሰልም፤ ትልቁን የአፍሪካን ድል ምድሯ ላይ በደማቅ ቀለም የፃፈች ናት፤ ሙሉ ታሪኩ ሲነሳ መንደርነቱ ተረስቶ የሀገር፤ የአህጉር፤ የጥቁር ሕዝቦች ድል ... ነው።

እምቢ ለሀገሬ፤ ለነፃነቴ በሚል በላቀ የሀገር ፍቅር ስሜት ከመድፍ ጋር በጎራዴ የተፋለሙበት፤ ለጓጉለት ነፃነታቸው በባዶ እግራቸው በተራራና በጢሻ እየሮጡ ሕልማቸው ላደረጉት ድል ሁለንተናቸውን መስዋዕት አድርገው የከፈሉበት ነው። የዓድዋ መዝሙር ባለቤቷ፣ የሙዚቃዋ ንግሥት እጅጋየሁ የተዋደቁት ለነፃነትና ለፍትሕ ልዕልና፣ ሰው ለመሆን ለክብር ነው ትለናለች፣ "ሰው" የሚለው ቃል ሁለንታዊ መሆኑን ልታጠይቅ።

"ሰው ክቡር" ስትል ደግሞ የሰው ክብሩ ከነፃነቱ ይጀምራል ልትለን ስለወደደች ነው? በነፃነት መኖር ሰዋዊና ሕሊናዊ ነው። እምቢኝ ያሉት አባቶች ገድል የተፃፈበት የሰው መሆን ክቡርነት የተገለፀበት የእንቢታ ማሳያና ውጤት ነው- ዓድዋ ።

ለሰው መሆን ክብር ዓድዋ ላይ "ሰው"ን ሰው ለማድረግ ሰው ሞቷል፤ ለመንፈስ ልዕልና ሕይወቱን በጦር ሜዳ ገብሯል፤ ደሙን ሜዳ ላይ አፍስሷል። ወርቅ የሆነ ሰው በእሳት አልፎ፣ አፈር ሆኗል፤ ይህ ሁሉ ግን ሌሎችን ወርቅ አድርጎ ለማኖር የቻለበት ድል ሆኖ ዘወትር ይዘከራል።

«የተሰጠኝ ሕይወት ዛሬ በነፃነት፣ ሰው ተከፍሎበታል ከደምና ከአጥንት» ትላለች! ያንን የደም ዋጋ፣ ያንን ታላቅ ተጋድሎ፣ ያንን በደማቁ ታሪክን የፃፈ ደም በእጅጋየሁ ሽባባው እንዲህ ስትገልፀው።

«በደግነት፣ በፍቅር፣ በክብር ተጠርቶ፤ በክብር ይሄዳል፤ ሰው ሊኖር ሰው ሞቶ» ... ዓድዋ የመስዋዕትነት ታሪክ ነው ነፍስን ለሌሎች ነፍስ የመስጠት መስዋዕትነት። ይህንን የሚያደርግ ደግሞ የጀግና ልብ ነው፤ ሩቅ ተመልካች ዓይን። የከበረች ምድሩን አሳልፎ የማይሰጥ ክንድ፤ የነፃነቱ ምልክት የባንዲራው ቀለም በልቡ የታተመ፤ ስለዚህ ሕልሙ ሀገሩ፤ ክብሩም ነፃነቱ የሆነ።

ሲጠቀለል የዓድዋ ጦርነት መነሻ ምንጩ "አትንኩን!" ነው። "አትንኩን" ባይሆንማ ቤቱ ተቀምጦ ባልተነካ!..."አትንኩን!" ያለው ግን ትግራይ ያለው ወገኑ ሲነካ ስላመመው ነው፤ ሰሜኑ፣ ደቡቡ፣ ምሥራቁ፣ ምዕራቡ ሲነካ "አትንኩን!" ብሎ በቁጣ ቤቱን ጥሎ ወጥቷል። ይህ ውለታ ያልጠፋት ከያኒ እንዲህ ታቀነቅናለች።

ዓድዋ ተራራው -ዓድዋ - ሰማዩ ፣ ሰማዩን የሰማው የተራራው ከንፈር ... ከውስጡ የሚመነጨው የትዝታ ገሞራ - ፊታውራሪ ገበየሁ - ገብቶ ሲነድድ - መዓዛው ለዛሬ ጣፋጭ- የነፃነት ዜማ ... የባርነት ስርየት ነው

በዛሬው የነፃነት ዜማ፣ በሀገር አደባባዮች ላይ ለመቆም ትናንት የተከፈለ ውድ ዋጋ አለ፤ ሰው የተባለ ውድ ዋጋ። ዛሬ ላይ ጥሩ የነፃነት መዓዛን ለመተንፈስ ያስቻለ ትናንት የከሰለ የወገን አፅም ነበር። በዚያ የውጊያ ሜዳ ላይ የብዙ ጀግኖች አጥንት እንደ ችቦ ነዷል፤ ያ የብርሃን ወጋገን ግን ዛሬ በጸና ሥነልቡናዊ ማንነትና ክብር ሁላችንንም አቁሞናል።

እጅጋየሁ ሽባባው ለዚህ ምስክሯ የዓይን እማኝ ብላ የጠራቻት ዓድዋ ናት እያለችን ነው።... ዓድዋ ተራራው -ዓድዋ - ሰማዩ ፣ ሰማዩን የሳመው የተራራው ከንፈር ... ከውስጡ የሚመነጨው የትዝታ ገሞራ - ፊታውራሪ ገበየሁ - ገብቶ ሲነድድ - መዓዛው ለዛሬ ጣፋጭ- የነፃነት ዜማ ... የባርነት ስርየት ነው። የመትረየስ እሳት ምላስ ያነደደው ተራራ፣ አፈሩን የዛቀው መድፍ ግራና ቀኙን የተጎሰመው ነጋሪት ድምፅ ያሸበረው ቁጥቋጦ የተሳከረውን ድብልቅልቅ ዋጋ፣ ስሌቱን የታሪክ ድርሳናት ብቻ ሳይሆኑ ዓድዋ ራሱ ይተርከው ብላለች።

ከያኒዋ «ትናገር ... ትናገር!» ያለችው ያኔ የነበረችው፣ ዛሬም በጉያዋ ስር ያንን ተዓምር ያቀፈችው እርሷ ናት!... የነደደ ፊቷ ... የከሰለ ልቧ ... ያንን ጠባሳ በእንባ እያጠቀሰ ሳይሆን በሳቅ እየፈካ ይናገረዋል!... እንባችንን አባቶቻችን አልቅሰው በሳቅ መንዝረው ሰጥተውናል! አፈር ሆነው ወርቅ አውርሰውናል!

እጅጋየሁ ሽባባው ዓድዋን እንዲህ ታሞካሻታለች፤

«ዓድዋ ዛሬ ናት ዓድዋ ትናንት፣
መቼ ተረሱና የወዳደቁት፡፡
ምስጋና ለእነሱ የዓድዋ ጀግኖች፣
ለዛሬ ነፃነት ላበቁኝ ጀግኖች፡፡
የጥቁር ድል አምባ ዓድዋ አፍሪካ እምዬ ኢትዮጵያ
ተናገሪ የድል ታሪክ አውሪ .... ዓድዋ »

በዜማ አቀንቅና አላበቃችም፤ ስለ ዋነኞቹ ጀግኖች አውስታለች፤"ምስጋና!" ብላ የክብር ዘውድ ደፍታላቸዋለች፤ አበባ ጉንጉን አጥልቃላቸዋለች፤ ሻማ ለኩሳለች።

የስንኟ ጅማሬ ከሰው ልጅ ጥቅም ተነስቶ ወደ ጥቁር ሕዝቦች ከዚያም ወደ አፍሪካ አፍንጫ ደርሷል፤ የድሉን አበባ እያሸተተች፣ ጀግኖች በነሰነሱት የነፃነት ጉዝጓዝ በክብር አዚማለች። ኢትዮጵያ የአፍሪካ-የጥቁር ሕዝቦች ከፍታ ችቦ ለኳሽ!... ታዲያ ይህን ታላቅ የአንድነት ዋጋን ዛሬ ላይ ጠብቆ የማቆየትን ቅኔ ሊቀኝ የሚሻ ሌላ ከያኒ እናጣ ይሆን? ልብ ያለው ልብ ይበልና ያቺን የጥቁር ፈርጥ አትዮጵያን ዳግም ወደ ከፍታ መንበሯ ለመመለስ የዘመን አርበኛ እንሁን እላለሁ።

ዜና

# ክልሉ የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን ለመመለስ እየሠራ ነው

ቃልኪዳን አሳዬ

አዲስ አበባ፡- የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን በፍትሐዊነት ለመመለስ በሚያስችል መልኩ እየሠራ መሆኑን የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል አስታወቀ፡፡

የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ጽሕፈት ቤት የመልካም አስተዳደርና አካባቢ ጉዳዮች ኃላፊ አቶ ካሳሁን ፍልፍሉ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ከዜጎች ጋር በቅርበት በመወያየት አቅም በፈቀደ መጠን የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን በፍትሐዊነት ለመመለስ እየተሠራ ነው፡፡

አቶ ካሣሁን በክልሉ ከሕዝብ ጋር የተጀመሩ ውይይቶች ሰፍተው እስከ ገጠር ቀበሌዎች እንደሚወርዱ ጠቁመው፤ በሕዝብና በመንግሥት መካከል አለመግባባቶች ካሉ ውጤታማ ሥራ ለመሥራት አዳጋች ስለሚሆን በየተቋማቱ ያሉ የመልካም አስተዳደር ችግሮች ተቆጥረው መታወቅና ምላሽ ማግኘት አለባቸው ብለዋል።

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ከተደራጀ በኋላ ለብዙ ዘመናት ይነሱ የነበሩ የአደረጃጀት ጥያቄዎች ምላሽ እንዲያገኙ በማድረግ በልማት ሥራዎች ላይ ማተኮር አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት የተለያዩ በዞን የመደራጀት ጥያቄዎች በሙሉ እንዲመለሱ መደረጉንም አንስተዋል፡፡

የመንግሥት አሠራር ለሕዝብ ግልጽና ተጠያቂነትን



አቶ ካሣሁን ፍልፍሉ

የሚያሰፍን መሆን እንዳለበት የሚገልጹት አቶ ካሣሁን፤ የመልካም አስተዳደር ችግር የማይገባበት ቦታ የለም። ተቋማት በልማት ፍትሐዊነት፣ በሥልጣን ክፍፍል፣ በአገልግሎት አሰጣጥ ላይና በሌሎችም ጉዳዮች የእቅዳቸው አካል ሊያደርጉት ይገባል ብለዋል፡፡

ችግሮችን ነቅሶ አውጥቶ እልባት በመስጠት ዜጎች ተረጋግተው ከመንግሥት ጋር በመሆን ልማትን እንዲያሳልጡ እየተሠራ ይገኛል ሲሉም አክለዋል፡፡

የመንግሥት ተቋማት በውስጣቸው ከሚያስተዳድሯቸው ሠራተኞች ጀምሮ ቅሬታዎችን በማዳመጥና በግልጽ በመወያየት ችግሮችን መፍታት አለባቸው የሚል መርሕ ተይዞ እየተሠራ እንደሚገኝ ያመላከቱት ኃላፊው፤ የመንግሥት ሠራተኛው ቅሬታ ይዞ ሕዝብን በደስታ ላገልግል ማለት የማይችል በመሆኑ ተቋማት ከውስጣቸው ጀምሮ እየሠሩበት ይገኛሉ ብለዋል፡፡

ክልሉ ከኬንያ ጋር በሚዋሰንባቸው አካባቢዎች በአርብቶ አደሮች ላይ የሚደረጉ ትንኮሳዎች እንዲሁም ከብት የመነጣጠቅና ከድንበር ጋር የተያያዙ የተለያዩ አለመግባባቶች መኖራቸውን ጠቁመው፤ በሀብት ምክንያት የሚፈጠሩ አለመግባባቶች ወደአላስፈላጊ መቃቃር አምርተው የንብረት ውድመትና የዜጎች መፈናቀል እንዳይከተል በሠላም መፍታት በሚቻልባቸው ጉዳዮች ላይ እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በ12 ዞኖች 32 ብሔር ብሔረሰቦችን ያቀፈው የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በይፋ የተመሠረተው በ2015 ዓ.ም ማገባደጃ ላይ መሆኑን ያወሱት አቶ ካሣሁን፤ አደረጃጀቱ እራሱ የመልካም አስተዳደር ጥያቄ መልስ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡



ምክትል ኮማንደር ማርቆስ ታደሰ

## ሿሿ - የነዋሪዎች ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በኋላ ግን ነገሩ መቀየሩን ተረዳች፡፡

ወደ ታክሲው ስገባ ዝምታና ከፍተኛ የሲጋራ ሽታ ነበር የምትለው ወጣት ገነት፤ ከመገናኛ ጎላጎል እንደደረሱም የዘረፋ ተግባራቸውን እንደጀመሩ ትናገራለች፡፡ የታክሲው ሾፌር በአካባቢው ሰው መኖሩን አለመኖሩን ካጣራ በኋላ ለእኩይ ተግባር አጋሮቹ ምልክት ይሰጣል፡፡

በዚህ ጊዜ ነበር ከኋላዋ ተቀምጦ የነበረው ተባባሪ አንገቷን በማነቅ በስለትና በመድኃኒት አስፈራርቶ ሞባይል ስልክ፣ 10 ግራም የአንገት ሐብል እንዲሁም 200 ብር የነጠቃት፡፡

ወጣት ገነት ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በታክሲዎች ለመንቀሳቀስ የድሮው አይነት በራስ መተማመን እንደሌላት ትናገራለች፡፡ ከድርጊቱ በኋላ ለተለያየ ሥነ ልቦናዊና አካላዊ ጫናም ተጋልጣለች፡፡

የመኪናውን ሰሌዳ ቁጥር በመያዝ አቅራቢያው ወደሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ በመሄድ ጥቆማ ብታቀርብም ያለብን ጉዳይ ብዙነው በሚል ምላሽ መፍትሔ ሳይሰጣት እንደቀረች ትጠቁማለች፡፡

ከንብረቱ መጥፋት በላይ በፖሊስ በኩል የተሰጠኝ ምላሽ የበለጠ የደኅንነት ስጋት እንዲሰማኝ አስገድዶኛል ባይ ናት፡፡

ፖሊስ መርምሮ ወንጀለኛውን ለማቅረብ ሰዎች መሞት አይጠበቅባቸውም የምትለው ወጣት ገነት፤ ሕዝቡ በፀጥታ አካላት ላይ እምነት እንዲኖረውና ይህንን እኩይ ተግባር የሚፈጽሙ አካላት ከሥራቸው እንዲታቀቡ ለወንጀሉ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት መሥራት እንዳሚያስፈልግ ትመክራለች፡፡

ከአጎና ሳሪስ እየተጓዝኩ ትራፊክ ሊቀጣኝ ነው ውረጂ በሚል ማዋከብ የሞባይል ስልኬን ቀሙኝ ያለችው ደግሞ ወጣት የምሥራች ደስታ ናት (ስሟ የተቀየረ)፡፡

የወንጀል ድርጊቱ የግለሰቦችን ሕይወት ያመሰቃቅላል የምትለው ወጣት የምሥራች፤ ወቅቱ ሥራ ፈላጊ የነበርኩበት ጊዜ በመሆኑ ለከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጫና አጋልጦኛል ትላለች፡፡

የሥራ እድል ፈጠራ ውስንነት፣ የፀጥታ አካላት ከኅብረተሰቡ ለሚቀርበው ጥቆማ ተገቢውን ምላሽ የማይሰጡ በመሆኑ፣ የፖሊሶች ስምሪት ውስንነትና ማኅበረሰቡ ድርጊቱን በጋራ አለማውገዝ ለጉዳዩ መባባስ ምክንያት ሆኗል ትላለች፡፡

የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ምክትል ኮማንደር ማርቆስ ታደሰ በበኩላቸው፤ ተቋሙ በተለምዶ ሿሿ እየተባለ የሚጠራው የወንጀል ድርጊት የሚፈጽሙ ግለሰቦች በቁጥጥር ሥር እያዋለ ይገኛል ይላሉ፡፡

ፖሊስ ግንባር ቀደም ከሚሠራቸው ሥራዎች አንዱ ወንጀል መከላከል ነው የሚሉት ምክትል ኮማንደሩ፤ በተለይ ተሽከርካሪዎች ላይ ትኩረት በማድረግ ከታኅሣሥ ወር ጀምሮ ወንጀለኞችን ለሕግ የማቅረቡ ጉዳይ ተጠናክሮ እንደቀጠለ ይናገራሉ፡፡

ድርጊቱ በከፍተኛ ሁኔታ እየቀነሰ የመጣ ቢሆንም ሙሉ በሙሉ ለማስቀረት ተጨማሪ ሥራዎች ይጠይቃልም ነው የሚሉት፡፡

ኅብረተሰቡ በየጊዜው ለሚደረገው የወንጀል መከላከል ተግባር ለፖሊስ ተባባሪ መሆን እንዳለበትም ምክትል ኮማንደሩ ይገልጻሉ፡፡

የፖሊስ አካላት በአግባቡ ጥቆማችንን አልተቀበሉንም በሚል ለተነሳው ቅሬታም፤ ፖሊስ ጣቢያዎችም ሆኑ የፖሊስ አባላት ጥቆማዎችን ተቀብለው ተገቢውን ምላሽ መስጠት ይጠበቅባቸዋል ሲሉ ተናግረዋል፡፡ ይህንን በማያደርጉ አካላት ላይ እርምጃ ይወሰዳልም ብለዋል፡፡

## ከንቲባ አዳነች አቤቤ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ባለዘጠኝ ወለል የመኖሪያ ቤት ሕንፃ ግንባታ በትናንትናው እለት የመሠረት ድንጋይ በማስቀመጥ ግንባታውን በይፋ አስጀምረዋል።

የጋራ መኖሪያ ቤት ግንባታውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከሜድሮክ ኢንቨስትመን ግሩፕ ጋር በመተባበር የሚገነባው መሆኑም ተገልጿል።

የግንባታው ሥራውን በአጭር ጊዜ በማጠናቀቅ ለልማት ተነሺዎች የሚረከብ መሆኑም ታውቋል።

በመዲናዋ የመኖሪያ ቤት ችግርን በዘላቂነት ለመፍታት በትኩረት እየተሠራ መሆኑን የገለጹት ከንቲባዋ በቀጣይም ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን አረጋግጠዋል።

ለነዋሪዎች እየተላለፉ የሚገኙ የጋራ መኖሪያ ቤቶችም ደረጃቸውን የጠበቁና የአዲስ አበባ ከተማን ደረጃና ውበት የሚመጥኑ መሆናቸውን ተናግረዋል።



## በ132 ሺህ ጣቢያዎች...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በዘንድሮው ዓመት ለመትከል ከታቀዱ ችግኞች መካከል 60 በመቶ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያላቸው እንደሚሆኑ በመግለጽ፤ ከቀሪ 40 በመቶ የደን ችግኞች ውስጥ 25 በመቶው በዓባይ ተፋሰስ ለመትከል መታቀዱን ጠቁመዋል፡፡

ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያላቸው ውስጥ የሚካተቱት የፍራፍሬ፣ የከብት መኖ፣ የቀርከሀ፣ የከተማ ውበት ዛፎች ናቸው፤ እነዚህም በችግኝ ጣቢያዎች እየለሙ ይገኛሉ ብለዋል፡፡ ለደን ሽፋን የሚውሉ ችግኞችም በተመሳሳይ እየለሙ መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

በሀገሪቱ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር በመጀመሪያና ሁለተኛ ምዕራፍ 50 ቢሊዮን ችግኝ ለመትከል ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን የገለጹት አቶ ፋኖሴ፤ ባለፉት አምስት ዓመታት 32 ነጥብ 5 ቢሊዮን ችግኝ ተተክሏል ብለዋል፡፡

በመጪዎቹ ሦስት ዓመታት ውስጥ ቀሪ 17 ነጥብ 5 ቢሊዮን ችግኝ እንደሚተከሉ ጠቅሰው በጥራት ላይ በማዘንበል የታቀደውን ለማሳካት ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በክረምቱ መርሐ ግብር ሥነ ሕይወታዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ የአረንጓዴ ዐሻራ ሥራዎች እንደሚካሄዱ ጠቅሰው፤ ለችግኞች ሥነ ምሕዳርን መሠረት ያደረገ የመትከያ መሬትና ችግኝ ጣቢያዎችን የማዘጋጀት ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሥራ የዝግጅት፣ የትግበራና የማጠቃለያ መርሐግብር ተከፍሎ ዓመቱን ሙሉ የሚሠራ መሆኑን በመግለጽ፤ የችግኞችና የችግኝ ጣቢያዎች ዝግጅት ማስፋፋት አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ኅብረተሰቡ የተፋሰስና የአረንጓዴ ዐሻራ ልማትን በውድድር መንፈስ እየተገበረው እንደሚገኝም ጠቅሰዋል።

## የቀጣናውን ሀብት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

አሏት የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ የቀደመ ሥልጣኔ፣ በሕዝቦች መካከል የሚጋሯቸው በርካታ ማኅበራዊ መስተጋብሮች፣ በተለያዩ ጊዜያት የነበሩ የዲፕሎማሲ ግንኙነቶች፣ የጂኦግራፊካል አቀማመጥ እንዲሁም ቅርስና ታሪክ ከሚነሱ ነጥቦች መካከል ተጠቃሽ መሆናቸውን ያብራራሉ፡፡

የባሕር በር ለማግኘት ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያለው ተፈጥራዊና ሰው ሠራሽ የጉርብትና ነጥቦችን ነቅሶ ማውጣትና ማስተዋወቅ ተገቢ እንደሆነ ረዳት ፕሮፌሰር አደም ምክረ ሃሳባቸውን ያቀርባሉ፡፡

ኢትዮጵያ በቀጣናው የሚገኙ ሀብቶች በጋራ ለመጠቀም የምታደርገው ጥረት እንደ ጸብ አጫሪነት መቆጠሩ የኔ ብቻ ከሚል ስግብግብነት የመነጨ እንጂ ስምምነቱ ለቀጣናው የበለጠ ኢኮኖሚያዊ ትስስር የሚፈጥር ነው ባይ ናቸው።

ኢትዮጵያ በታሪክ ለአፍሪካ አንድነትና ነፃነት ያበረከተችው አስተዋፅዖ እንዲሁም በዓለም መድረክ መፍጠር የቻለችው ተፅዕኖ እንደ መልካም አጋጣሚ መጠቀም ያስፈልጋልም ሲሉ ያስረዳሉ።

ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገራት ጋር ከኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ግንኙነት በተጨማሪ በባሕል፣ በቋንቋ፣ በእሴት እንዲሁም በአኗኗር ዘይቤ ጠንካራ ግንኙነት አላት ያሉት ደግሞ በእንጅባራ ዩኒቨርስቲ የሶሺዮሎጂ መምህር አንተሁነኝ ብርሃኑ ናቸው፡፡

ኢትዮጵያ ከጎረቤቶቿ ጋር ዕውቀትን ልምድን ተሞክሮንና ሀብቶችን በጋራ ለመጠቀም የሚያስችል ተፈጥሯዊ ግንኙነት አላት የሚሉት መምህሩ፤ የማኅበረሰብ ጥናት ከሚያሳያቸው በርካታ ጉዳዮች በተጨማሪ ለብዙ ዓመታት የቆየ ታሪካዊ ዳራ ያለው መልካም ግንኙነት የማይዘነጋ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

እንደ መምህር አንተሁነኝ ከሆነ፤ ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገራት ጋር የምትጋራቸው ባሕል፣ እሴት፣ ወግ፣ ልማድ፣ ታሪክ፣ ቋንቋ እንዲሁም የጂኦ-ፖለቲካል አቀማመጥ በቀጣናው ያሉ ሀብቶች በጋራ ለመጠቀም የሚያስችላት ነው፡፡

በጎረቤት ሀገራት መካከል ልዩነት ላይ የሚያተኩሩ ጉዳዮች የሉም የሚሉት መምህሩ፤ ከፖለቲካዊ ግንኙነቱ በተጨማሪ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቱ ማሳደግ እንደሚገባ ይመክራሉ፡፡

ምሑራኑ እንዳመላከቱት፤ መልካም የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት የበለጠ ለማሳደግ የባሕል፣ የቋንቋና የልምድ ልውውጥ መድረኮች ማስፋፋት ይገባል፤ የቀጣናውን ማኅበረሰብ በቀላሉ በማገናኘት የኢትዮጵያንና የጎረቤቶቿን የጋራ ተጠቃሚነት ለማሳደግ የሚደረገውን ጥረት ያጠናክራል።

# የፀጥታ ችግር ያልበገረው የክልሉ ግብርና ሥራ

**ማህሌት አብዱል**



በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች የተነሱ አለመረጋጋቶችና የፀጥታ ችግሮች ለአጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ተግዳሮት ሆነው ቆይተዋል። በተለይም ለአብዛኛው ኢትዮጵያዊ የኑሮ መሰረት የሆነው ግብርና ከሰላም ውጭ የሚታሰብ አይሆንም። ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ አገሩና ቀየው ሠላም ሊሆን የግድ ነው። በዚህ ረገድ በተለያዩ ምክንያቶች በአገሪቱ የተፈጠረውና እየተፈጠረ ያለው የሰላምና ጸጥታ ችግር አርሶአደሩን ጨምሮ መላውን ሕዝብ የችግሩ ገፈት ቀማሽ እንዲሆን አድርጎታል። የሰላምና ፀጥታ ችግር ፈተና ከሆነባቸው ክልሎች አማራ ክልል አንዱ ነው። በክልሉ አብዛኛው ማኅበረሰብ አርሶአደርና በግብርና ላይ የተመሰረተ ሕይወት ያለው እንደመሆኑ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የችግሩ ተቋዳሽ እንደነበረ ታይቷል።

የሰላምና ፀጥታ ችግር የልማቱ ማነቆ ሆኖ እንዳይቀጥል ክልሉ ብርቱ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል። በተለይም በዘንድሮ የበልግ ወቅት የእርሻ ሥራው እንዳይስተጓጎል ብርቱ ጥረት መደረጉ ነው የተገለጸው። የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ መረጃ እንደሚያሳየው፤ የግብርና ሥራውን ሊያደናቅፉ የሚችሉ ማናቸውንም ችግሮች ለመፍታት ብርቱ ጥረት እየተደረገ ነው፤ በዚህም አበረታች የሚባል ውጤት እየተመዘገበ ነው የሚገኘው። በክልሉ በተለይም የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት 22 ዞኖች እና ከተማ አስተዳደሮች፣ በሁሉም ወረዳ በሚባል ደረጃ እንዲሁም በሁለት መስኖ ፕሮጀክቶች የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት እየተከናወነ ይገኛል። ይህ ዘገባ እስከተጠናከረበት ጊዜ ድረስ 140 ሺ 700 ሄክታር መሬት በስንዴ ዘር ተሸፍኗል። 193 ሺ 611 ኩንታል ምርጥ ዘር ጥቅም ላይ ውሏል። ከ429 ሺ በላይ አርሶአደሮች በበጋ ስንዴ ልማት ተሳታፊ ሆነዋል።

በሌላ በኩል ባለፈው ዓመት ከሰላም እጦትና ከተለያዩ ችግሮች ጋር በተገናኘ በተፈጠረው የማዳበሪያ ግዢ መዘግየቱ ይታወሳል። ይህ ችግር ደግሞ ከምርትና ምርታማነት መስተጓጎል ባሻገር ለመልካም አስተዳደር እና ተያያዥ ችግሮች ምክንያት ሆኖ ቆይቷል። የፌዴራል መንግስት ካለፈው ዓመት ተሞክሮ በመነሳት የማዳበሪያ ግዢን ቀድሞ በመፈፀም ክፍተቱን ለመሙላት ጥረት ሲያደርግ እንደነበርም ይታወቃል።

በተመሳሳይ በአማራ ክልል በርካታ አካባቢዎች የተፈጠረውን የፀጥታ ችግር ተከትሎ ማዳበሪያን በወቅቱ ለተጠቃሚው አርሶአደር ለማድረስ ችግሮች አጋጥመውት እንደነበርም ታይቷል። የክልሉ ግብርና ቢሮ መረጃ እንደሚያመላክተውም፤ የክልሉ መንግስት ዘንድሮ የማዳበሪያ አቅርቦቱ ከወትሮው በተለየ ፍጥነት ለአርሶአደሩ ተደራሽ ለማድረግ እየሰራ ይገኛል። ከፌዴራል መንግስት ጋር በመተባበርም ከጥቅምት ወር መጨረሻ ጀምሮ ወደ ሃገር ውስጥ መግባት የጀመረውን ማዳበሪያ በፍትሃዊነት በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች እንዲሰራጩ ርብርብ በማድረግ ላይ ይገኛል።

እንደመረጃው ከሆነ በዚህ ዓመት የተፈፀመ የማዳበሪያ ግዢም ባለፈው ዓመት ከተፈፀመው ግዢ የሶስት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ኩንታል ብልጫ አለው። አሁን የክልሉ ድርሻ የሆነው አንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን በላይ ኩንታል ማዳበሪያ ወደብ ላይ ሲገኝ በቀጣዮቹ ጊዜያት ከወደብ ወደ ማዕከል ይደርሳል ተብሎ ይጠበቃል። በዚህ ረገድም በክልሉ የማዳበሪያ አቅርቦቱን ተደራሽ ለማድረግ ከወደብ ወደ ማዕከላት የሚያጓጉዙ 14 የትራንስፖርት ማኅበራት አሉ።

የክልሉ ግብርና ቢሮ የሕዝብ ግኑኝነት ኃላፊ አቶ አምሳሉ ጎባው በተለይም ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዳስታወቁት፤ ክልሉ ካለፈው ዓመት ተሞክሮ በመነሳት የግብርና ሥራው ማነቆ የሆነ የፀጥታና ከዚያ ጋር ተያያዥ የሆኑ ችግሮችን ለመፍታት ከሚመለከታቸው የፀጥታ አካላት ጋር ተቀናጅቶ ርብርብ በማድረግ ላይ ይገኛል። በዋናነትም የማዳበሪያና የዘር አቅርቦቱ በተሳለጠ መልኩ ለሁሉም የክልሉ አካባቢዎች ተደራሽ ለማድረግ ትኩረት አድርጎ እየሰራ ነው።

ለአርሶ አደር በክልሉ አንዳንድ ቦታዎች ላይ በሚስተዋለው የፀጥታ ችግር ሳይዘናጋ የበልግ ልማቱን እንዲያከናውን አስፈላጊው ድጋፍ እየተደረገለት መሆኑን ኃላፊው ይናገራሉ። በዋናነትም ከዚህ ቀደም ቅሬታ ይነሳበት የነበረውን የማዳበሪያ አቅርቦት ችግር ለመፍታትና ለአርሶአደሩ ተደራሽ ለማድረግ ከፌዴራል መንግስትና ከፀጥታ አካላት ጋር በቅንጅት እየተሰራ ስለመሆኑ ያስረዳሉ። «በክልላችን በ2016/17 የምርት ዘመን ከአምስት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ሄክታር መሬት በላይ በዘር ለመሸፈንና 160 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማምረት እቅድና ግብ አስቀምጠን እየሰራን ነው» ይላሉ።

ለዚህ ደግሞ በ2016/17 የመኸር እርሻ ሥራ ስምንት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ በፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር ተገዝቶ ከወደብ ላይም እየደረሰ መሆኑን ያስረዳሉ። በቀጣዮቹ ቀናት ለአርሶአደሩ ተጨማሪ ማዳበሪያ ተደራሽ ለማድረግም በአሁኑ ወቅት ከወደብም ወደ ክልል በመጓጓዝ ላይ ይገኛል። በተጨማሪም በክልሉ በሚገኙ የአርሶአደር ዩኒየኖችና ማኅበራት ደርሶ ለአርሶአደሩም እየተሰራጨ ሲሆን ይህም በበጋ መስኖ ልማት ሥራው ትልቅ አስተዋፅኦ ይኖረዋል ተብሎ የሚጠበቅ እንደሆነ ነው ያብራሩት።

«ዘንድሮ የመስኖ ልማታችንን በተመለከተ ደግሞ ከ333 ሺ ሄክታር መሬት በላይ አምርተን 40 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለመሰብሰብ አቅደን እየሰራን ነው» የሚሉት ኃላፊው፤ ከዚህም ውስጥ ደግሞ 250 ሺ የበጋ መስኖ ልማት መሆኑን ነው ያመለከቱት። በተያያዘም ከዚህ ቀደም በነበሩት ዓመታት የማዳበሪያ ችግር በክልሉም ተከስቶ እንደነበር አስታውሰው፤ ክልሉ ይህንን ችግር መሻገር የሚያስችሉ ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴዎችን ማድረጉን ይጠቅሳሉ። «ከዚህ በፊት የአፈር ማዳበሪያ ግዢ የሚፈፀመው የካቲት፤ መጋቢትና ሚያዚያ ወር ላይ ነበር፤ አሁን ግን ከጥቅምት ጀምሮ ግዢ በፌዴራል ደረጃ መፈፀሙ ከምርት ወቅቱ ቀደም ብሎ ሥራዎችን በማከናወን ምርታማነትን በተጨባጭ ለማረጋገጥ እያገዘን ነው» በማለት ይናገራሉ።

ይህ ብቻ ሳይሆን ማዳበሪያ ወደ ሃገር ከገባም በኋላ በቀጥታ ለአርሶአደሩ ተደራሽ የማድረጉ ሥራ ሰፊ ርብርብ እየተደረገበት እንደሆነ ይጠቁማሉ። በተለይም የፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር ከፀጥታው አካል ጋር በመነጋገር ካለው የፀጥታ መናጋት ችግር ጋር ተያይዞ ማጓጓዝ የሚያስችል ሁኔታ ለመፍጠር በትብብር ሥራው እየተሰራ ነው ሲሉ ይጠቅሳሉ። «በፀጥታ ምክንያት አንዳንድ ቦታዎች ላይ ባይስተካከል ኖሮ ከዚህ በፊት ፈጥኖ ይገባ ነበር። ግን የፀጥታው ጉዳይ የራሱ አሉታዊ ሚና ነበረው። ቢሆንም ግን አሁን በምርት ዘመኑ ሥራ ተጀምሯል። ጥሩ ደረጃ ላይ ነው ያለው» ሲሉም ያክላሉ።

እንደ ኃላፊው ገለፃ፤ ክልሉ በመስኖና በበልግ የምርት ወቅት ያለውን አቅም አሟጦ በመጠቀም በምርት ዘመኑ የተሻለ ውጤት እንዲገኝ እየሰራ ነው። በዋናነትም የክልሉ ግብርና ቢሮ እንደአጠቃላይ ሁሉንም የክልሉ አካባቢዎች ተደራሽ የሚያደርጉ የድጋፍ ሥራዎችን አጠናክሮ ቀጥሏል። የማዳበሪያ ስርጭቱ በአሁኑ ወቅት በምስራቅ አማራ፤ ወልዲያ፣ በደሴ፣ ጎንደር፣ እንዲሁም ወደ ጎጃም የተለያዩ አካባቢዎች መሄድ በሚገባው ልክ ባይሄድም በተቻለ መጠን ከፀጥታ አካል ጋር በመናበብ ተደራሽ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ነው ያለነው።

ይሁንና ማዳበሪያም ሆነ የዘር አቅርቦቱ በፍትሃዊነት ተደራሽ የማድረጉ ሥራ የሁሉም አካላት ብርቱ ትብብር ይፈልጋል የሚል እምነት እንዳላቸው ኃላፊው ይናገራሉ። «ምክንያቱም ደግሞ ከ80 በመቶ በላይ የሚሆነው የክልሉ ሕዝብ አርሶአደር ነው። የኑሮ መሰረቱም ግብርና ነው፤ ግብርና ለገበሬው ሕይወቱ፤ ሥራው ነው። በመሆኑም የሁልም አካላት ያልተቋረጠ ርብርብ ይፈልጋል» ይላሉ። በዚህ ረገድም አርሶአደሩ ትኩረቱን የግብርና ሥራው ላይ ብቻ በማተኮር ለምርታማነትና ውጤታማነት እንዲተጋ ቢሮው የበኩሉን ጥረት እያደረገ ይገኛል።

ግብርና ወቅት ጠብቆ የሚሰራ እንደመሆኑም ወቅቱ ካለፈ አርሶአደሩ ብቻ ሳይሆን ሌላው ሕዝብ አደጋ ውስጥ ይወድቃል። በመሆኑም አርሶአደሩ ሰላማዊ ምኅዳር ተፈጥሮለት በተረጋጋ መንፈስ ልማቱን እንዲከውን የክልሉ መንግስትም ሆነ የፀጥታ አካሉን የበኩላቸውን ድጋፍ እያደረጉ ስለመሆናቸው ያስረዳሉ። «የግብርና ሥራ የጊዜ ጥገኛ በመሆኑ ያንን ስራ የሚያስተጓጉል ማንኛም አካል ከዚህ ተግባሩ ሊታቀብ ይገባል። የሚጎዳው ደግሞ ከማንም በላይ አርሶአደሩን ነው። ይህን ማስረፅና ከእኛ የሚጠበቅ ሥራ ነው» ሲሉም ያስገነዝባሉ።

ቢሮው በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች በፍትሃዊነት ተደራሽ ለማድረግ ታሳቢ አድርጎ በሚሰራባቸው አካባቢዎች የማይናቅ ውጤት እያገኘ መሆኑን ይጠቁማሉ። የማዳበሪያ ፍላጎት መፍጠር፤ የባለሙያዎችን ዝግጁነት ማረጋገጥ፤ የሙያና ቴክኒክ ስልጠና መስጠት ማቀድ ሥራዎችን ሲሰራ ቆይቷል፤ በዚህም የተሻለ ውጤት እያገኘን ነው ያለነው» ይላሉ። ይሁን እንጂ የፀጥታ ጉዳይ የቢሮው ብቻ የሚሰራ ባለመሆኑ ከባለድርሻ አካላትን ቀጣይነት ያለው ድጋፍ የሚሻ መሆኑን ነው ያመለከቱት።

በሌላ በኩልም የክልሉ መንግስት በድርቅ የተጎዱና ውሃ አጠር አካባቢዎች ላይ በፌዴራል መንግስት ከሚሰራው የድጋፍ ሥራ ጎን ለጎን ቢሮው ድርቅ መቋቋም የሚቻልባቸውን ማካካሻ እቅድ በማቀድ ራሱን የቻለ ግብረኃይል ተቋቁሞ እየተሰራ መሆኑን ይናገራሉ። «የተጎዱ አካባቢዎች ወደነበረበት ለመመለስ ቢሮው የበኩሉን ስራ እየሰራ ነው። ይህም ቢሆን ክልሉ በመደበኛ በጀት የሚያከናውነው ሥራ አይደለም፤ የሌሎች ባለድርሻ አካላትን ቅንጅታዊ ጥረት የሚጠይቅ ነው፤ በዚህም የተገኘው ውጤት አበረታች ነው» ሲሉ ያስረዳሉ።

አክለውም «እርግጥ የፀጥታ ችግር ፈታኝ እንደነበር ይታወቃል፤ ግን አርሶአደሩ ባኅል አድርጎ ስለያዘው ዘንድሮ ሰፊ ንቅናቄ ተፈጥሮ ነው እየተሰራ ያለው» ይላሉ። ዘንድሮ የተፋሰስ ልማት ሥራው ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩና ሌሎች የክልሉ ባለስልጣናት በተገኙበት በደቡብ ወሎ በሰፊ ንቅናቄ መጀመሩንና ወደ ሌሎች አካባቢዎችም በማስፋት ከእርሻ ስራው ጎን ለጎን እየተካሄደ መሆኑን ይጠቁማሉ። ከዚህ ቀደም በነበረው ጊዜ ሁከትና ግጭት በሚኖርበት ወቅት የለሙ ተፋሰሶች መቃጠል፤ መቆረጥ፤ መውደም ያጋጥም እንደነበር አስታውሰው፤ «አሁን ግን በክልሉ አንዳንድ ቦታዎች ላይ አለመረጋጋቱ ቢኖርም በአንፃሪያዊ ሁኔታ ተፋሰሶች ተጠብቀው ነው ያሉት» በማለት ያስረዳሉ።

በተመሳሳይ የግብርና ኤክስቴንሽን ስራም ለችግሩ ሳይበገር እየተከናወነ መሆኑን ጠቅሰው፤ «በዚህም ከዚህ ቀደም ማዳበሪያ አልፈልግም ይል የነበረው አርሶአደር ዛሬ ላይ አምጡ እያለ እኛኑ ማፋጠጥ ይዟል፤ ይህም የመጣው በተሰራው ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ ነው» ሲሉ ያብራራሉ። ያም ቢሆን ግን በየትኛውም አካባቢ በታቀደው ልክ ተንቀሳቅሰን ሰርተናል ማለት አይደለም፤ ከእቅዳችን አንፃር ብዙ ይቀረናል፤ ለዚህ ደግሞ የሁሉም የክልሉ ነዋሪና ባለድርሻ አካላት ድጋፍ ያስፈልጋል በማለት አስገንዝበዋል።

ከሁሉ በላይ ግን በቀጣዮቹ የምርት ጊዜያት የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦቱ በፍትሓዊነት ተደራሽ እንዲሆን ከፍትሕ፤ ከፀጥታ አካላት ጋር በጋራ መስራት ይጠበቃል። ለዚህ ደግሞ የሚዲያ ተቋማትም ሚናቸውን ሊወጡ እንደሚገባ ኃላፊው አስገንዝበዋል። «ምክንያቱም የአርሶአደሩ ጉዳት ዞሮ ዞሮ የማይነካው አካል የለም፤ ጦርነት ከጨረሰው በላይ ረሃብ የሚጨርሰው ስለሚበልጥ ርብርቡ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት። አማራ ክልል ሰላም ሳይኖር ኢትዮጵያ ሰላም ናት ሊባል አይችልም፤ በመሆኑም እንደሃገር በሁሉም አካበቢዎች ላይ ሰላም እንዲሰፍንና ገበሬው እርሻው በተሳካ ሁኔታ እንዲያካሂድ ስለሰላም መስበክ ሁላችን የድርሻችን ልንወጣ ይገባል» ሲሉ አሳስበዋል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

# የመምህራን እጥረትና የትምህርት መሰረተ ልማት ችግር

ግርማ መንግሥቴ

ልማት በየፈርጁ ነው። የሰው ኃይል ልማት፣ መሰረተ ልማት ወዘተ እያለ እንደሚሄደው ሁሉ የመምህራን ልማትም እንደ ሌሎቹ ሁሉ በጥብቅ ከተያዙትና የሚመለከታቸው አካላት የዕለት ተዕለት ክትትል ከሚያደርጉባቸው እንቅስቃሴዎች አንዱ ነው።

የመምህራን ልማት በይዘቱም ሆነ አቀራረቡ ዓለም አቀፍ ገፅታ ያለው ሲሆን፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የትም አገር ያለና እየተተገበረ ያለ ነው። በተለይ አሁን ባለንበት ዘመን ጉዳዩ ልዩ ትኩረትን ከማግኘቱም በላይ የተሻለ ትውልድን ከመፍጠርና ዘመኑን ያገናዘበ ትምህርትን ተደራሽ ከማድረግ አኳያ በቀላሉ ሊታለፍ የማይችል ሆኖ ተገኝቷል።

ወቅታዊ መረጃዎች እንደሚያሳዩት የትምህርት ጉዳይ አሳሳቢ እየሆነ የመጣው አንድ ቦታ ብቻ አይደለም፤ ወይም በሰሜን እና በደቡብ ብቻ አይደለም ችግሩ ያለው። በምስራቅና ምዕራብም የተወሰነ አይደለም። ከማዕከላዊው የዓለማችን ክፍል ጀምሮ በአራቱም ማዕዘን ትምህርትና ጥራቱ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሰዋል፤ የዓለምንም የጋራ ጥረት እየጠየቀ ነው።

በዓለም አቀፍ ደረጃ የመምህራንን ቁጥር እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ ሲመጣ አይታይም። ለዚህ ማሳያው ደግሞ እ.ኤ.አ ከ2000 እስከ 2019 ባለው ጊዜ ውስጥ 50 በመቶ በመጨመር ከ62 ሚሊዮን በመስፈንጠር 94 ሚሊዮን (11.6 ሚሊየን በቅድመ አንደኛ ደረጃ፤ 32.6 ሚሊየን በአንደኛ ደረጃ፤ 20.7 በመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ፤ 15.7 ሚሊየን በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ፤ እና 13.1 ሚሊየን በሶስተኛ ደረጃ) ላይ ደርሷል።

ምርጥ ስርአተ ትምህርት አላት የምትባለውንና በመምህራን ልማት የማትታማውን አሜሪካ ስንመለከት አጠቃላይ የመምህራኖቿ ቁጥር 4 ሚሊዮን 007 ሺህ 908 ሲሆን፤ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በየዓመቱ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ተማሪዎች ተመዝግበዋል።

በዚያው ልክ ደግሞ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ 81 ከመቶ የአንደኛ ደረጃ፤ 78 ከመቶ የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ሙያው ከሚፈልገው ዝቅተኛውን ደረጃ የያዙ ናቸው። ከሰሀራ በታች ያለውን ሲታይ ደግሞ 65 ከመቶ የመጀመሪያ፤ 51 ከመቶ ሁለተኛ ደረጃ መምህራን ዝቅተኛውን መስፈርት ይዘው ይገኛሉ።

በዚሁ በጥር ወር ይፋ በሆነው የዩኔስኮ ጥናት ላይ እንደተመላከተው፣ ጥናቱ ከተካሄደባቸው አገራት አንዷ በሆነችው አሜሪካ 163,650 (5 በመቶ) አካባቢ የሚሆኑ መምህራን ከሰለጠኑበት የትምህርት መስክ ውጪ በማስተማር ላይ ያሉ ሲሆን፣ እነዚህ መምህራን ያለ ሙያቸው ማስተማራቸው ብቻ ሳይሆን አጫጭር ስልጠና እንኳን ያልወሰዱና ሰርተፊኬት ሳይቀር የሌላቸው መሆናቸው ነው።

መረጃው እንደሚለው እ.ኤ.አ በ2030 በዓለም አቀፍ ደረጃ የተቀመጠውን ግብ ለማሳካት ለመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት 69 ሚሊዮን አዳዲስ መምህራን ያስፈልጋሉ። የሴት መምህራን ቁጥር ዝቅተኛ በሆነባቸው፣ ከሰሀራ በታች ያሉ አገራት በዚሁ ዓመተ-ምህረት የተያዘውን ግብ ለማሳካት 15 ሚሊዮን መምህራንን መቅጠር ግዴታቸው ነው። ከእነዚህ አሃዞች ውስጥ ኢትዮጵያ የድርሻዋን መውሰዷ የግድ ነውና ጉዳዩን አርቆ ማየት አያስፈልግም።

አንድ UIS (2016)ን ጠቅሶ ለንባብ የበቃ ሰነድ እንደሚያመለክተው ዓለማችን ከፍተኛ የሆነ የመምህራን እጥረት ያለባት ሲሆን፣ በተለይ ከሰሀራ በታች ያሉት አገራት ከልክ በላይ ለችግሩ ተጋልጠው ይገኛሉ። እንደዚሁ ጥናት ግኝት ከሆነ በቀጠናው በሚገኙት አገራት ያሉ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 70 ከመቶ የሚሆኑት በከፍተኛ የመምህራን እጥረት የተጎዱ ሲሆኑ፤ በእነዚሁ አገራት የሚገኙ 90 ከመቶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለከፍተኛ የመምህራን እጥረት ችግር ተጋልጠው ይገኛሉ። ይህ ማለት አሁን ካሉት በተጨማሪ የሰለጠኑና ብቃት ያላቸው መምህራን እንደሚያስፈልጉ ነው።

በአፍሪካ ያለው ሁኔታ ደግሞ ከዚህም በላይ ያስደነግጣል። በአሁኑ ሰዓት አንድ አራተኛ የመጀመሪያ ደረጃ፤ ከሁለተኛ ደረጃ ደግሞ 50 በመቶ የሆኑት ብቻ በመምህርነት ሙያ ሰልጥነው በማስተማር ተግባር ላይ ያሉ ናቸው። ይህም “አፍሪካ ዓለም አቀፍ ግዴታ የሆነውን አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን እ.ኤ.አ በ2030 እውን ማድረግ ካለባት አህጉሪቱ በሙያው የሠለጠኑ 17 ሚሊዮን መምህራን የምታስፈልጓት መሆኑ፤ እነዚህ መምህራንም ብቃትና ጥራት ብቻ ሳይሆን፣ ብቃትና ጥራታቸውን ተከትሎ ጥሩ ደመወዝና ምቹ የሥራ አካባቢዎች የሚያስፈልጓቸው መሆኑ ነው።

የ26 ስቴቶች አቃፊ፣ ከዓለም ሰባተኛና 214 ነጥብ 3 ሚሊዮን (እ.ኤ.አ በ2021 ጥናት) ሕዝብ ቁጥር ወዳላትና ደቡብ አሜሪካዊት ወደ ሆነችው፤ እንዲሁም፣ ዓለም በጥቅጥቅ ደን ባለቤትነቷ ወደሚያውቃት ብራዚል ስንሄድም የመምህራን በተለይም የእንግሊዝኛ መምህራን እጥረት በከፍተኛ ደረጃ የሚታይ ሲሆን፤ ምክንያቶቹ የንግድ መስፋፋት፣ የቱሪዝም ሴክተሩ መበልፀግና የመሳሰሉት ሲሆኑ፣ የእነዚህና ሌሎች ዘርፎች ከፍተኛ የተማረ የሰው ኃይል መፈለግ ትምህርትን እጅጉን አስፈላጊ አድርጎታል። በመሆኑም፣ የመጀመሪያ ዲግሪ (ቢኤ ዲግሪ) ያለው ሲበዛ ተፈላጊና ዘና ብሎ በሚኖርባት ብራዚል ከፍተኛ የመምህራን እጥረት፤ እንዲሁም ከፍተኛ የሆነ የመምህራን ልማት አስፈላጊነት ይስተዋላል።

በቂ መረጃ በሚገኝባቸው አገራት፣ የመምህራንን አጠቃላይ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሙያዊ ደረጃን በተመለከተ አገራት የተዘረዘሩ ሲሆን፣ በቻይና፣ ግሪክ፣ ቱርክ እና ደቡብ ኮሪያ መምህራን ከፍተኛ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ላይ ሲገኙ፤ በጣሊያን፣ ቼክ ሪፐብሊክ፣ ብራዚል እና እስራኤል ደግሞ በተቃራኒው ደረጃ ላይ ናቸው።

አውሮፓዊቷ ሉክሰምበርግ ለመምህራን የተሻለ ደሞዝ (አንድ የባችለር ዲግሪ ባለቤት ገና ሲቀጠር በዓመት €67,000 (US $70,323.20) ይከፈለዋል) በመክፈል ከዓለም የመጀመሪያዋና ፊት መሪ ስትሆን፤ ከአፍሪካ “ጥሩ ከፉይ” (በዓመት ከ$22,000 እስከ $46,000) በሚል የተመደበችው ደግሞ ደቡብ አፍሪካ ነች። ሉክሰምበርግ አንድ መምህር 30 ዓመት ካገለገለ ደሞዙ €119,000 (US $124,902.40) ሊደርስ የሚችልባት አገርም በመሆኗ እስካሁን አቻ አልተገኘላትም።

“ታላቁ መምህር" የሚል ማኅበራዊ ማዕረግን ካገኘው ሶቅራጥስ ጀምሮ ከበሬታን በተመለከተም እንደዚሁ የተደረጉ ጥናቶች ያሉ ሲሆን፤ በጥናቶቹ ላይ ሰፍሮ እንደሚነበበው ከሆነ ቻይና መምህራን በከፍተኛ ደረጃ (መቶ ከመቶ) የሚከበሩባት አገር ስትሆን፣ ማሌዥያም 93 ከመቶ መምህራን የሚከበሩባት አገር በመሆን በሁለተኛነት ደረጃ ላይ ትገኛለች።

ይህንን እዚህ ማቅረባችን የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ የመስሪያ ቤታቸውን የ6 ወራት የስራ አፈፃፀም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሀሙስ የካቲት 7/2016 ዓ.ም ባቀረቡበት ወቅት “የመምህርነት ሙያን የሚቀላቀለው ሰው በእጅጉ እየቀነሰ ነው፤ የመምህራን ጉዳይ የጥራት ብቻ ሳይሆን አሁን በቅርብ ባደረግነው ጥናት ያየነው በቅርብ ጊዜ ከፍተኛ የሆነ የመምህራን እጥረት ይገጥመናል፤ ለዚህ እንደ ምክንያት የተነሳው የደመወዝ ክፍያው ከሙያው ጋር የሚመጥን ባለመሆኑ ነው" ማለታቸውን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው።

የካቲት 1 ቀን፣ 2016 ዓ.ም በዋና መስሪያ ቤቱ ስብሰባ አዳራሽ፣ መምህራንን እና የትምህርት ቤት አመራሮችን በተመለከተ ስላዘጋጃቸው መመሪያዎች ማስተዋወቅን አስመልክቶ በተደረገ ውይይት ላይ በመጪው ክረምት ባሉበት የትምህርት ደረጃና በሚያስተምሩት የትምህርት አይነት ስነ ዘዴ ላይ የተመሰረተ፤ “ልዩ የአቅም ማጎልበቻ” ስልጠና በስራ ላይ ላሉ መምህራን ሊሰጥ መሆኑን፤ መመሪያዎቹ የአጠቃላይ ትምህርት መምህራን የደረጃ እድገት አፈጻጸም፣ የትምህርት ቤት አመራሮች ምልመላ እና ምደባ እንዲሁም የእጩ መምህራን ምልመላ እና መረጣን የሚመለከቱ መሆናቸው በትምህርት ሚኒስቴር የመምህራን እና የትምህርት ልማት ዴስክ ኃላፊ ወይዘሮ አሰግድ ምሬሳ ተነግረዋል።

ከዚህ ቀደም “በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት በመላው ሀገሪቱ ለሚገኙ መምህራን ለሚያስተምሩት የትምህርት ዓይነት ብቁ ሆነው እንዲገኙ የሚያስችል የሥራ ላይ ስልጠና በመስጠት የብቃት ማረጋገጫ እንዲያገኙ ይደረጋል"።

የመምህራንና ትምህርት አመራሮች ልማት ሥራ አስፈጻሚ ሙሉቀን ንጋቱ (ዶ/ር) ለኢፕድ እንደ ተናገሩት ማለቱ የሚታወስለት ትምህርት ሚኒስቴር መመሪያዎችን ከማሻሻል በተጨማሪ የመምህራን እና የትምህርት ቤት አመራሮችን አቅም ለማሳደግ ከላይ በተጠቀሰው መርሀ-ግብር ከ15 እስከ 20 ለሚሆኑ ቀናት “በተመረጡ ዩኒቨርሲቲዎች” እንደሚሰጥ የሚጠበቀው ይህ ስልጠና፤ ይበልጡን ትኩረት የሚያደርገው “የሁለተኛ ደረጃ የሳይንስ እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርቶች ላይ” መሆኑም ተገልጿል። በሂደት ሁሉንም፣ በየደረጃው ያሉትን መምህራን ሁሉ እንደሚያካትትም እንደዛው ተነግሯል።

700 ሺህ የሚደርሱ መምህራን እንዳሉ በሚነገርባት ኢትዮጵያ መምህራኑ ስልጠናውን ሲያጠናቅቁ ሰርተፊኬት የሚሰጣቸው ሲሆን፣ ብሔራዊ ፈተና በማዘጋጀት የመምህራንን አቅም ለመፈተሽ እየተሠራ እንደ ሆነም ከላይ በጠቀስናቸው የስራ ኃላፊ ተገልጿል። ተግባሩ “ኢዱኬሽን ዴቨሎፕመንት ትረስት" እና ከመሳሰሉት ጋር በመተባበር፣ ከ2013 ዓ.ም አንስቶ እየተከናወነ መሆኑ፤ በ2015 በጀት ዓመት 728 የሚሆኑ ሴት መምህራኖችን ወደ አመራርነት ለማምጣት የሚያስችል ስልጠና መስጠቱም ተመላክቷል።

እንደ ዶ/ር ሙሉቀን ማብራሪያ ከዚህ በፊት በተሰጡ የሥራ ላይ ስልጠናዎች በሀገር አቀፍ ደረጃ አምስት ሺህ የትምህርት አመራሮች ስልጠናቸውን አጠናቀው ሰርተፍኬት ተበርክቶላቸዋል።

ትምህርት ሚኒስቴር በበኩሉ እንደሚለው ባለፉት 30 ዓመታት የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ጥራት ወርዷል። ትምህርት የአገር የሉዓላዊነት እሴት መለኪያ መሆኑ እየታወቀ በዚህ ጉዳይ ለዓመታት ተቀልዷል። እርስ በርስ መነጋገር ሁሉ የማይቻልበት ሁኔታ ላይ ተደርሷል። በኢትዮጵያ የትምህርት ዘርፉ ከ10 ዓመታት በኋላ ትምህርት ቤቶች እንደ አሁኑ የፀብ (የረብሻ) መፍለቂያ ሳይሆኑ የመወዳደሪያና የብቃት ማጎልበቻ ይሆናሉ።


ከዚህ በኋላ እንደ ከዚህ ቀደሙ ዲግሪ እንደ ከረሜላ የሚታደልበትን አሠራር አስቀርቶ፣ በብቃት እና በችሎታ ብቻ ዜጎች ማዕረግ የሚያገኙበት ሥርዓት በዘላቂነት ይዘረጋል። ይህ ለመሆኑ አንዱ ምክንያት ምናልባትም ዋናው የመምህራን ልማትን የተመለከተ ይሆናል በሚል ይመስላል፤ በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ስርነቀል እርምጃዎችን እየተወሰደ ይገኛል። ከእነዚህ መካከል ቀደም ሲል፣ በኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ያሉ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው 124 የትምህርት ክፍሎች ተጨፍልቀው ወደ 56 ዝቅ እንዲሉ የተደረገው ውሳኔ ይጠቀሳል። ነሐሴ 18 ቀን 2015 ዓ.ም. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ 30ኛውን ዓለም አቀፍ የትምህርት ጉባዔ ባካሄደበት ወቅት “የትምህርት ቤቶች ርዕሳነ መምህራን ከአሁን በኋላ በካድሬነት ሳይሆን በብቃታቸው ብቻ የሚመረጡ መሆኑን" አስታውቋል።

በዚህ መሠረት ትምህርት ሚነስቴር በአገር አቀፍ ደረጃ በብቃታቸውና በችሎታቸው የተመዘኑ 1ሺህ 600 የትምህርት አስተዳዳሪዎች ሥልጠና የተሰጣቸው መሆኑን ተናግሯል። ትምህርት ቤቶችን በግብዓትና በጥራት ከማሻሻል ባሻገር ክህሎት፣ ብቃትና ችሎታ ባላቸው ርዕሳነ መምህራን እንዲተዳደሩ ማድረግ ትልቁን ድርሻ እንደሚይዝ ገልጿል። የትምህርት ቤቶችን ደረጃ ከማሻሻል በተጨማሪ ተማሪዎቻቸውን በዕውቀት ተወዳዳሪ ማድረግ የሚችሉ መምህራንን ማብቃት ከተያዙ ግቦች መካከል አንዱ መሆኑን አስታውቋል።

በመምህራን ልማት ያለው ችግር እንዳለ ሆኖ በትምህርት ተቋማት መሰረተ ልማት ላይም ተመሳሳይ ችግር ይታያል። የጉዳዩ ባለቤት የሆነውና ባለፉት 30 ዓመታት የትምህርት ጥራት ወድቋል የሚለው ትምህርት ሚኒስቴር ባለፈው ሐምሌ ወር ላይ እንደተናገረው በኢትዮጵያ ካሉ 50 ሺህ ትምህርት ቤቶች ከፊሉ፣ በጥራታቸው ከደረጃ በታች ሲሆኑ፤ ትምህርት ቤቶቹ፣ አስፈላጊው መሠረተ ልማት የሌላቸው፤ ለመማር ማስተማር ምቹ ያልሆኑ ናቸው።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ፣ “በኢትዮጵያ ካሉት 50 ሺ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከ71 በመቶ በላይ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ከ86 ከመቶ በላይ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ ለመማር ማስተማር ሂደት የማይበጅ ከባቢ ያላቸው፣ በጥራታቸውም ከደረጃ በታች ናቸው" የሚለው ተቋሙ፣ በትምህርት ሚኒስትር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ አማካኝነት፣ የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል፣ የእነዚህን ትምህርት ቤቶች ደረጃ ማሳደግ እንደሚያስፈልግና ይህንንም ለማከናወን፣ ሀገራዊ የሕዝብ ንቅናቄ እንደሚጀመር፤ በኅብረተሰብ ተሳትፎ የትምህርት መሠረተ ልማትን ለማሻሻል በሚደረገው ሀገራዊ ንቅናቄ፣ በአምስት ዓመት፣ የሁሉንም ትምህርት ቤቶች ደረጃ ለማሻሻል እንደታቀደም አመልክቷል።

ይህ ጽሑፍ፣ እኛም የዓለም አካል ነንና፣ ባለፈው ዓመት ዩኔስኮ፣ ዩኒሴፍ፣ ዓለም አቀፍ ትምህርት (EI)፣ እና ዓለም አቀፍ የስራ ድርጅት (ILO) በጋራ ያዘጋጁት “ዓለም አቀፍ የመምህራን ቀን"ን አስመልክቶ የተቀመረውን መሪ ሃሳብ (“The teachers we need for the education we want: The global imperative to reverse the teacher shortage") መሰረት አድርገን ስንመለከተው ይዞት የተነሳው ሀሳብ ቀላል አለመሆኑን መገንዘብ አይከብድም። በተለይም እጥረት (shortage) በቁጥር ብቻ ሳይሆን በጥራትና አቅምም መሆኑን፤ እሱም መቀልበስ ያለበት መሰረታዊ ዓለም አቀፍ ችግር መሆኑን ልብ ስንል የጽሑፉ ወቅታዊነትና ተከታታይ ሆኖ የመቆየቱን አስፈላጊነት እንረዳለንና ጉዳዩን አጀንዳ ለማድረግ መጣራችን ተገቢ ነው።



ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ

# ‹‹ በዓድዋ የተገኘውን ድል የሀገራችንን ሰላም በማስጠበቅ ልናስቀጥለው ይገባል ››

-አቶ ግርማ ቸሩ- በሰላም ሚኒስቴር የመንግስታት ግንኙነት ዴስክ ኃላፊ

እፀገነት አክሊሉ

ሰላም የሁሉ ነገር ዋስትና ነው። ሰርቶ የመለወጥ፣ ወልዶ የማሳደግ፣ ወጥቶ የመግባት፣ ዘርቶ የማፍራት በአጠቃላይ በሰው ልጆች የዕለት ተዕለት ተግባር ውስጥ ከምንተነፍሰው አየር ያልተናነሰ ዋጋ አለው። ሰላም ከሌለ ነገ የለም። ስለ ነገ ማሰብም ማቀድም የሚቻለው በሰላም ውስጥ ነው። የሰላምን ምንነት ለመረዳት ሰላም የግጭትና ጦርነት አለመኖር፣ በሰዎች መካከል የመቀራረብ፣ የመግባባትና ግጭቶችን በንግግር የመፍታትና የመምራት ሁኔታን ይመለከታል።

ሰዎች ከራሳቸውና ከአካባቢያቸው ጋር ሰላም ኖሯቸው ለጋራ እድገትና አብሮ መኖር አስተዋጽኦ ካደረጉ ሰላም አለ ማለት ነው። በእያንዳንዱ ሕብረተሰብ ዘንድ ውስጣዊና ውጫዊ ስምምነት ካለ ሰላም አለ ለማለት ይቻላል። ስለዚህ ሰላም ከፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ኑሮ ባሻገር ሰዎች ከሰዎች፣ ከተፈጥሮና ከአካባቢ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ስለሚመለከት ሰላም ሁሉን አቀፍ ይዘት አለው ማለት ነው።

በኢትዮጵያ ታሪክ ግጭቶች ሌላ ግጭት እየወለዱ የግጭት አዙሪት ውስጥ ተነክረን ሰላም አልባ ዘመናትን አሳልፈናል። ለዘመናት ሲዘሩ የቆዩ የጥላቻና የመከፋፈል ዘሮች ፍሬ አፍርተው ሕብረተሰባችንን ያስተሳሰሩት ክሮች እየላሉና እየተበጣጠሱ የመጡበትና ግጭት የተንሰራፋበት ስለሆነ ከበድ ያሉ መንገራገጮች ላይ ደርሰናል። በርካታ መስዋዕትነቶችንም እንደሀገር እየከፈልን ነው። ይህም “ምክንያታዊ“ ሆነን ሰላምንና የሰላምን መንገድ መውሰድ አማራጭ የሌለው መሆኑን ያሳየናል።

ይህ ሰላማችን በተለይም ባለፉት አባቶቻችን የአንድነትና የመደማመጥ አብሮ የመኖር፤ ጠላትን በጋራ ክንድ ድባቅ የመምታት አቅም ላይ ተመስርቶ ዛሬ ላይ ያጣነውን ሰላም እንመልስ ዘንድ ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ምሁራንን የአገር ሽማግሌዎችና ሌሎችንም በአንድ በማድረግ " አድዋን ለዘላቂ ሰላምና ለጠንካራ ሀገረ መንግስት ግንባታ " በሚል ርዕስ የውይይት መድረክ አዘጋጅቶ የትላንቱን ዓድዋ ከዛሬ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማገናኘት ብዙ ሀሳቦች ተሰንዝረዋል ። በተለይም ዓድዋ የአንድነታችን ማሳያ ነው በሚል ዛሬ ላይ ያለንበት አስከፊ የመከፋፈል ሁኔታን የሚለውጡ ሃሳቦችም ተንጸባርቀዋል።

ዓድዋ ኢትዮጵያውያን በዘር በሀይማኖት ሳይከፋፈሉ የእድሜና የፃታ ልዩነት ሳያደርጉ ሆ ብለው በመነሳት እስከ አፍንጫው በዘመናዊ ጦር የታጠቀን የጠላት ሰራዊት ድል የመቱበት ነው። ይህንን የመሰለ ከእኛ አልፎ የዓለም ሕዝብ ያደነቀው ታሪክ ባለቤት ሆነን ሳለን ግን ዛሬ ላይ በመንደርና ጎጥ ተከፋፍለን እርስ በእርሳችን ችግር ውስጥ መግባታችንም ለቀጣዩ ትውልድ አሳፋሪ ገድልን እንደማቆየት ነው የሚሉ ሃሳቦች በስፋት ተንሸራሽረዋል።

እኛም ከውይይት መድረኩ ተሳታፊ ከሆኑት መካከል በሰላም ሚኒስቴር የመንግስታት ግንኙነት ዴስክ ኃላፊ ከሆኑት ከአቶ ግርማ ቸሩ ጋር ቆይታን አድርገናል።



**አዲስ ዘመን ፦ ዓድዋን እንዴትና በምን መልኩ ይገልጹታል**

**አቶ ግርማ ፦** ዓድዋ ለእኛ ምን ማለት እንደሆነ ለማብራራት ብዙ መድከም አያስፈልግም፤ ምክንያቱም ሁሉም ኢትዮጵያዊ የራሱ ስም ያህል የዓድዋን ምንነትና ማንነት ጠንቅቆ ያውቀዋልና። ይህ ሁኔታም ከትውልድ ትውልድ እየተሸጋገረ የመጣ ታላቅ ድል ከመሆኑ ጋር በተገናኘ ከብዙ ጉዳዮች ጋር አገናኝተንም መመልከት እና መተንተን እንችላለን።

ዓድዋ የኢትዮጵያውያንን አገር ወዳድነት አጠናክሮ ያለፈ ትልቅ ድል ነው። ይህ ድል ደግሞ አሁን ላለው ትውልድ የሚያስተላልፈው ትልቅ መልዕክት አለ፤ በተለይም አባቶቻችን ዘመናዊ የጦር መሳሪያን እስከ አፍንጫው የታጠቀውንና በዘመናዊ ወታደራዊ ስልጠና የተዘጋጀውን ኃይል በነበራቸው ባሕላዊ መሳሪያ በእግራቸው ብዙ ኪሎ ሜትሮች ተጉዘው በጋማ ከብቶቻቸው ድል የነሱበት ነው። እዚህ ላይ ግን ልብ ሊባል የሚገባው ነገር በወቅቱ ሕዝቡ በቂ ወታደራዊ ስልጠና እንዲሁም ዘመናዊ መሳሪያ አልፎ ተርፎም የሚያስፈልገውን ትጥቅና ስንቅ ማግኘት ባይችልም ቅሉ በነበረው ቆራጥነት እንዲሁም አንድነት ድሉ የኢትዮጵያውያን ሆኗል። ይህ ልዩነትን ወደጎን አድርጎ በአንድነት መትመምና መዝመት ለዛሬው ትውልድ የሚያስተላልፈው መልዕክት በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

ይህ ትውልድ ከድሉ ሊወስደው የሚገባው ትምህርት ቢኖር እንደ አገር በተለይም በአሁኑ ወቅት አንድ እንዳንሆን እያደረጉን ያለው ተግዳሮት ምንድን ናቸው? የሚለውን መመልከት ይመስለኛል። ለዚህ መልሱ ደግሞ ድህነታችን ነው። ድህነቱ የሚፈጥራቸው ነገሮች ደግሞ እዚህም እዚያም ሰዎች በፖለቲካ ወግነው በቡድን ተለያይተው እንዲጋጩ ምክንያት ሆኗል። በመሆኑም ያኔም የእርስ በእርስ ቅራኔዎች ሳይኖሩ ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ ሆኖ አልነበረም ድሉ የመጣውና አሁንም ቅራኔዎቻችን ላይ ትኩረት በመስጠት ቁጭ ብለን ለመወያየት በመሞከርና በተረጋጋ መንፈስ አንድነታችንን ማጠናከር የጋራ የሆኑ ችግሮቻችንን በአንድነት መንፈስ መፍታት የዓድዋ ድል አንኳር መልዕክት ነው።

**አዲስ ዘመን ፦ ኢትዮጵያውያን ከዓድዋ መንፈስ በተጻራሪ በአንድነት መቆም ለምን ተሳነን?**

**አቶ ግርማ ፦** የሚገርመው ነገር ያን ጊዜ ለዓድዋ ጦርነት መነሻው የባዕድ ወረራ ነው። ነገር ግን ዛሬ በዚህ መልኩ እርስ በእርሳችን ችግር ውስጥ ለመግባታችን የውጭ ኃይሎች እጅ የለበትም ለማለት እቸገራለሁ። ውስጣዊ ችግሮቻችን በርካታ መሆናቸው ይታወቃል። እነዛን ችግሮች የምንፈታበት መንገድ ደግሞ በውጪም በውስጥም ላሉ የተለያዩ አካላት መንገድ የሚከፍት በመሆኑ ለችግሩ አጋልጦናል ብዬ አስባለሁ።

በአገራችን ውስጥ የተለያየ የፖለቲካ እሳቤ፣ አመለካከት ያላቸው ብሔሮችና ብሔረሰቦችና የፖለቲካ ኃይሎች አሉ። በነገራችን ላይ እንደዚህ አይነት ሃሳቦችና ፖለቲካዊ አመለካከቶች ቀድሞም ቢሆን አልነበሩም ማለት አይቻልም። አባቶቻችን ብዙ ቅራኔዎች ነበሩባቸው፤ ነገር ግን ሁሉንም ልዩነታቸውን አስወግደው ወደአንድነት ነው የሄዱት። እንደዚሁ ሁሉ አሁንም ለውጭ ኃይሎች ተጋላጭ በሚያደርጉን የውስጥ ችግሮቻችን ላይ ቁጭ ብለን ተነጋግረን መፍታት ላይ ደካማ መሆናችን የፈጠረውን ችግር እንዲሁም ውጤቱንም እያየነው ነው።

በመሆኑም ትውልዱ ሊያደርገው ይገባል ብዬ የማስበው ልዩነቶች ተፈጥሯዊ መሆናቸውን በመገንዘብ ነገር እየመዘዙ ወደግጭት ከመሄድ ይልቅ በችግሮቹ ዙሪያ ቁጭ ብሎ መወያየት ጥያቄ ያለው የትኛውም አካል ደግም በቀናነት ጥያቄውን የማቅረብ መልስ ሰጪው አካልም በተመሳሳይ ለጥያቄው ዋጋ ሰጥቶ በአግባቡ የመመለስ ችግሮችን በኃይል ለመፍታት ከመሞከር ይልቅ እነዚህ አማራጮች መልካም ናቸው።

> **ዓድዋ ኢትዮጵያውያን በዘር በሀይማኖት ሳይከፋፈሉ የእድሜና የፃታ ልዩነት ሳያደርጉ ሆ ብለው በመነሳት እስከ አፍንጫው በዘመናዊ ጦር የታጠቀን የጠላት ሰራዊት ድል የመቱበት ነው**

**አዲስ ዘመን ፦ እንግዲህ ችግሮቻችንን በውይይት ለመፍታት ያስችለናል በማለት እንደ አገር የምክክር ኮሚሽን አቋቁመናልና ይህ ምን ያህል ችግሮችን ለመፍታት አቅም ይኖረዋል ይላሉ?**

**አቶ ግርማ ፦** የምክክር ኮሚሽኑ መቋቋሙ እንደ አገር ጥሩ አካሄድ ይመስለኛል። በምክክር ኮሚሽኑ አማካይነትም ያሉንን ኢኮኖሚያዊ፤ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ችግሮች ሁሉ አውጥተን በደንብ ተነጋግረን ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ ፈተን አንድነታችንን ለማጠናከር የሚኖረው ሚና በቀላሉ አይታይም።

ዛሬ ላይ እንደ ሀና ማህበራዊ ችግሮቹም ብዙ ናቸው፤ በመሆኑም ወጣቱ እንደ ወጣት ምሁራን የፖለቲካ ፓርቲዎች የአገር ሽማግሌዎችና ሴቶች በያገባኛል መንፈስ በአንድነት ሆኖ በችግሮቹ ላይ መወያየት ፤ተወያይቶም መፍትሔ ላይ መድረስ ይገባል።

ችግሮቻችንን የዚያ የዚህ እያልን ባለቤት እየሰጠናቸው በሄድን ቁጥር እየሰፉና እየተጋነኑ ከመሄድ ውጪ የሚያመጡት ፋይዳ ስለማይኖር ሁሉም የድርሻውን እየተወጣ መንግስትም የመሪነቱን ሚና እየተጫወተ በአገር ጉዳይ በተለይም አሁን ባለንበት አስቸጋሪ ሁኔታ ላይ ሁሉም የራሱን ድርሻ ሊወጣ ይገባል።

**አዲስ ዘመን ፦ ለአብዛኛው ችግሮቻችን ምክንያቶቹ የተዛቡ የታሪክ አረዳዶች ናቸው የሚሉ ብዙዎች ናቸውና የሰላም ሚኒስቴር**

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# ‹‹ በዓድዋ የተገኘውን ድል የሀገራችንን...

ከ9ኛው ገጽ የዞረ

**ያሉትን መዛነፎች ስማስተካከል ምን እየሰራ ነው**

**አቶ ግርማ ፦** አሁን ላይ እንደ አገር ከማያግባቡን ነገሮች መካከል ያለፈ ታሪክ ሳይሆን ትርክቶቹ ናቸው። ታሪክ ሊለወጥ የሚችል ነገር አይደለም። ማንም ያለፈን ታሪክ ወደኋላ ሄዶ መለወጥ አይችልም ፤ ነገር ግን እነዚያ ኩነቶች ሰዎች ጋር የሚደርሱበት ትርክት እየተዛባ እዚህ አድርሶናል። አሁን እንደ አገር የጀመርነው አገራዊ ምክክር መድረክ ጥሩ አጋጣሚ ነው። ምክክር መድረኩ በሚካሄድባቸው አካባቢዎች ሁሉ እነዚህ ነገሮች ተነስተው ሕዝብ በሚገባ ተወያይቶባቸው መግባባት ላይ ደርሶ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሊዘጋ ይገባል።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም ጉዳዩን ቀደም ብሎም በማንሳት እንደ አገር የማያግባቡን ነገሮች ምንድን ናቸው? በማለት የታሪክ ምሁራንን ከታሪክ አንጻር ያለውን ልዩነት እንዲፈቱ አንድ ላይ የማቀራረብ ስራ ሰርቷል። በሌላ በኩል ደግሞ በፊት አንድ ላይ ተቃራኒ የሆኑና ያልነበሩ ተጻራሪ ሀሳቦችን በታሪክ ትርክት መልክ ሲጽፉ የነበሩ ምሁራንን ሁሉ በአንድ መድረክ በማምጣት በአገር አቀፍ ደረጃ "የታሪክ ምሁራን ማኅበር " እንዲቋቋም በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ስራዎች ተሰርተዋል።

አሁን ላይ ማኅበሩ ወጥ የሆነ ታሪክና ትርክት ለመፍጠር ሙከራ እያደረገ ነው። በነገራችን ላይ ይህ ቀላል ነገር አይደለም፤ ተጠናክሮ በሄደ መጠንም ወደ መቀራረብ ወደ አንድነት አንድ ዓይነት ወደሆነ ታሪክ አረዳድ ያስገባናል ።

**አዲስ ዘመን ፦ የታሪክ ምሁራን ተሰባስበው በሕዝቡ ውስጥ አንድ ዓይነት የታሪክ አረዳድ እንዲኖር ስማድረግ ጥረት መደረጉም ሆነ የምክክር መድረኩ ችግሮቻችንን በመፍታት በኩል ሲኖራቸው የሚችለው ሚና ምን ያህል ነው ማለት ይቻላል?**

**አቶ ግርማ ፦** ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በዋና ዋና አገራዊ ጉዳዮች ላይ ሕዝቡ ተቀራራቢ ግንዛቤ እንዲኖረው ማስቻል በአዋጅ የተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት ነው። ይህንን ኃላፊነታችንን ለመወጣትም ወጣቶችን ሴቶችን ምሁራንን እንዲሁም ሌሎች ይመለከታቸዋል ያልናቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች በሙሉ በማሳተፍ ስልጠናዎችና የፓናል ውይይቶች እናደርጋለን። ይህ እንግዲህ የምክክር ኮሚሽኑም ከመቋቋሙ በፊት ጀምሮ ሲሰራ የነበረ ስራ ነው። ኮሚሽኑም ከተቋቋመ በኋላ አስፈላጊውን መረጃ እየሰጠን የመነሻ ሃሳቦችን እያበረከትን እንገኛለን። እዚህ ላይ ግን ሊታወቅ የሚገባው ነገር ኮሚሽኑ ገለልተኛ የሆነና በራሱ የሚሄድ መሆኑም ነው።

እንደ አንድ አገራዊ መግባባት ላይ እንደሚሰራ ተቋም ግን በአገራችን ያሉ አለመግባባቶች ለመፍታት በተለይም ያለፈው ታሪካችን ወደፊት ከሚኖሩን የጋራ ሕልሞቻችን ጋር ምን ማለት ናቸው? ያለፉት ታሪኮቻችን ላይ ምን ጥሩ ነገር አለ ? እንዲሁም የትኛው ነው መጥፎ የሚለውን በመለየት ከመለየትም በኋላ ታሪክ ታሪክ ነውና የሚፋቅ የሚሰረዝ ነገር አይኖረውምና ባሉት ሁኔታ ለአገር ግንባታ መዋል በሚችሉበት ሁኔታ መጠቀም ይገባል።

በሌላ በኩልም እነዚህ መጥፎ ፤ ጥሩ እያልን የምንከፋፍላቸውን ታሪኮቻችንን ተምረንባቸው የምናርመውን እያረምን፤ የምናሻሽለውን እያሻሻልን ከጥንካሬው ተምረን ደግሞ ልናስቀጥለው የሚገባውን በዛው ልክ እያስቀጠልን የምንሄድበት አግባብ ሊኖር ይገባል። '

ከዚህ አንጻር ሴክተራችን ታሪክን በማስተማር በማሳወቅ ብሎም ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎችና የሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅቶ የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት የግንዛቤ ፈጠራ ላይ ከፍ ያለ ስራን እየሰራ ነው። በዚህም ሁሉም የመንግስት መስሪያ ቤቶች ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ና ሌሎችም ለአገር ግንባታ የሚጠቅሙ እንደ ዓድዋ ያሉ ታሪኮችን በማንሳት ግንዛቤ በማስጨበጥ እንዴት ነው ለአገር ግንባታ ብሎም አሁን ከፊታችን የተደቀኑ ችግሮችን ልናልፍ የምንችለው በሚለው ላይ ትኩረት አድርገን በመስራት ላይ እንገኛለን።



**አዲስ ዘመን፦ ታሪክን ሃብት አድርገን ችግሩን በትምህርትነት ጥሩ ጎኑን ደግሞ በመልካምነቱ ተቀብለን ስትውልዱ ስማቆየት ከማን ምን ይጠበቃል?**

**አቶ ግርማ ፦** ይህ እንግዲህ የሁላችንም ኃላፊነት ነው። በተለይም የታሪክ ምሁራን ሰፊውን ድርሻ መውሰድ ቢገባቸውም እንደ አገርና ሕዝብ ግን ሁላችንም ታሪክ ሁነት በአንድ ወቅት የተከናወነ ነገር መሆኑ ማወቅና መረዳት ያስፈልጋል።

ታሪክን በዚህ መልኩ ከተቀበልን የተዛቡ ትርክቶቹን ማስተካከል ላይ ብዙ መሰራት ያለባቸው ጉዳዮች ስላሉ እንደ አገር የተቋቋመው የምክክር መድረክ ላይ ሁሉም ሰው በያገባኛል መንፈስ በጠንካራ ሁኔታ ተሳትፎ ሀሳቡንም አቅርቦ በታሪኮቻችን ላይ ተቀራራቢ ትርክት እንዲኖረን ማድረግ ይገባል።

ይህንን በምሳሌ ባስረዳሽ መኪና ሲነዳ በግንባር አልያም በጎን መስታወት ወደኋላ የሚታየው ወደፊት ለመሄድ ነው፤ ሁልጊዜ ወደኋላ አይኬድበትም ። በመሆኑም በመስታወቱ ወደኋላ እያየን ወደፊት በሄድን ቁጥር ያለፍነው መንገድ ምን አይነት ነው? የሚከተለን መኪና ፍጥነቱ ምን ይመስላል? የሚለውንና ሌሎች ነገሮችን ለማየት ነው። ታሪክንም ወደኋላ የምናየው ድክመትና ጥንካሬውን እያስተዋልን ወደፊት ለመጓዝ ነው። እዚህ ላይ ግን ወደኋላ አይተን ችግር ያልነውን ነገር ብቻ እየመዘዝን ዛሬ ላይ የምናመጣው ከሆነ ወደፊት በትክክል ለመሄድ የማንችልበት ደረጃ ላይ ከመድረሳችንም በላይ አደጋ ውስጥ የሚያስገባ ነው።

**የእርስ በእርስ ግንኙነታችንንም እያጠናከረ ወጣቶቹም በሄዱበት አካባቢ ስራ እየሰሩ ትዳር እየያዙና ቤተሰብ እየመሰረቱ ወደ አንድነቱ እየመጡ በመሆኑ ስራው ውጤታማና ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚገባው ነው**

ምሁራን ደግሞ እዛም እዚህም ተዛብተው የሚነገሩ የታሪክ ትርክቶችን የማቃናት ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው። ቀጥሎም የፖለቲካ ፓርቲዎች ትልቁን ኃላፊነት የሚወስዱ ሲሆን ምክንያቱ ደግሞ የሕዝቡ ጥያቄዎች ፍላጎቶችና አስተሳሰቦች በእነሱ በኩል ተቀናብረው ስለሆነ የሚመጡት በተቻለ መጠን እነሱም ታሪክን እያወቁ እንዳላወቁ በመሆን ለራስ ፍላጎት ብቻ በሚመች መልኩ እየተረኩ ሕዝቡን ወዳልሆነ አቅጣጫ ከመምራት መቆጠብ ይገባቸዋል።

አንዳንድ ነገሮቻችን አይነኬ እየሆኑ ነው በተለይም አትንኩኝ ወይም የእኔ ብቻ ነው ትክክል የሚለው ሃሳባችን ብዙ ዋጋ እያስከፈለን ነው። ለውጭ ጠላትም እያመቻቸን ነው። ይህንን በመገንዘብ አትንካኝ አልነካህም የሚለውን አስተሳሰብ ከውስጣችን ጠርገን አውጥተን የንግግር የውይይት ባሕል በልዩነቶቻችን ላይ የመነጋገር ሌላውን የመረዳት፤ የመገንዘብ ፤ በእሱ ቦታ ሆኖ የማየት፤ ወጣቶች ሴቶች ሁሉም የበኩሉን ሊወጣ ይገባል። ከዚህ አንጻር ሚኒስቴር መስሪያ ቤታችን በተለያየ ጊዜ በማኅበረሰብ ደረጃ ሰፋፊ የውይይት መድረኮችን እያዘጋጀ ስራዎችን እየሰራ ነው።

**አዲስ ዘመን ፦ እንደሚሰሩበትም ተቋም እንደ ግልምም እንደ አገር የገባንባቸውን ችግሮች ፈትተን፤ ተደማምጠንና ተሳስበን አንድነታችንን አጠናክረን በሰላም እንኖር ዘንድ መልዕክት ቢያስተላልፉ?**

**አቶ ግርማ ፦** ከሰላም ሚኒስቴር አንጻር የምጠቅሰው አገራችን ላይ በርካታ ፖለቲካዊ፤ ማኅበራዊ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ችግሮች አሉብን። በሌላ በኩል ደግሞ በተዛቡ አረዳዶች ከተለያዩ መንግስታት ሲንከባለሉ ቆይተው ዛሬ ላይ እኛ የተቀበልናቸው የማያስማሙን ታሪኮች አሉን፤ በመሆኑም ትውልዱ አደጋዎቹን በሚገባ መረዳት አደጋዎቹንም ለመሻገር ምንድነው ከእኔ የሚጠበቀው የሚለውን አጽዕኖት ሰጥቶ ማሰብ ይገባዋል።

በሌላ በኩል እኛ ኢትዮጵያውያን እስከ ዛሬ የደረስነውም ፍጹም በሆነ መደማመጥ ፤መከባበር፤ መዋደድና መተሳሰብ በመሆኑ አሁን ላይም ልዩነቶች እንኳን ቢኖሩን የቀድሞ አንድነትና ሕብረታችንን ፍቅራችንን በማሰብ ችግሮችን የመፍቻ መንገዶችን ከማንም ሳንጠብቅ እርስ በእርሳችን ተነጋግረን መፍታት ይገባናል።

በሰላም ሚኒስቴር በኩል አንድነታችንን ለማምጣት ከተለያዩ አካባቢዎች ወጣቶችን በበጎ ፈቃደኝነት በመመልመል ከአካባቢያቸው ውጪ ሄደው አገልግሎቶችን እንዲሰጡ የማድረግ ስራ አለ። ይህ ስራ ከምናገረው በላይ ውጤት ያመጣ ነው። በታሪክ ትርክት ላይ ያላቸው የተዛባ አስተሳሰብ ከትውልድ ቀያቸው ወጥተው ሌላ ቦታ ሲሄዱ ተቀይሯል። ስለዚህ ይህ ሁኔታ አንዳንድ ችግሮቻችንን እየፈታልን የእርስ በእርስ ግንኙነታችንንም እያጠናከረ ወጣቶቹም በሄዱበት አካባቢ ስራ እየሰሩ ትዳር እየያዙና ቤተሰብ እየመሰረቱ ወደ አንድነቱ እየመጡ በመሆኑ ስራው ውጤታማና ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚገባው ነው። ይህ እንደ ሰላም ሚኒስቴር በጥቂቱ የሚሰራ ነው ነገር ግን ሌሎች ሴክተሮች፣ ክልሎች ፣ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ሊሰሩበት የሚገባ ነው።

ትውልዱ በጥቃቅን ምክን ያቶች ለሚጠሉንና እድገታችንን ለማይፈልጉ ዱላ አቀባይ ከመሆን ይልቅ ተረጋግቶ አገሩን ማስቀደም ብሎም መሪውን ስለወደደ አልያም ስለጠላ ብቻ ሳይሆን አገሬ ምን ጊዜም የኔ ናት ብሎ ማሰብ ያስፈልጋል።

**አዲስ ዘመን ፦ ስነበረን ቆይታ በጣም አመሰግናለሁ**

**አቶ ግርማ ፦** እኔም አመሰግናለሁ

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## ንክር የሀበሻ ልብሶች

**ወርቅነሽ ደምሰው**

አሁን ላይ የአገር ባሕል አልባሳቶች ዘመኑን በሚፈልገው ልክ በተለያየ ዲዛይን ውብ በሆነ መልኩ ተሰርተው በተለያዩ አማራጮች እየቀረቡ ነው። በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎችም የአገር ባሕል አልባሳቶቹ በማንኛውም ሥፍራ ዘወትር መለበስ እንዲችሉ ቀላልና ምቹ በማድረግ እየተጠበቡበት ይገኛሉ።

እነዚሁ ልብሶች ታዲያ በአዘቦት ቀናት እና በበዓላት ወቅት በስፋት የሚስተዋሉ ሲሆን፤ አልባሳቱ በገበያ ላይም እንዲሁ ለሽያጭ ቀርበው እንመለከታለን። ይህም በብዙዎቻችን ዘንድ አግራሞትን የሚጭር በመሆኑ ‹‹እንደዚህ ውብ የሰውን ቀልብ የሚስቡ የኛው የአገር ልብሶች ናቸው እንዴ!›› በማለት ራሳችንን እንድንጠይቅ ያስገድዱናል።

እነዚህን የሀገር ኩራት የሆኑ ውብና ማራኪ የሀበሻ ልብሶች በዓለም ላይ እንዲተዋወቁና ዓለም አቀፍ ተቀባይነት አግኝተው በዓለም ገበያ ላይ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ መስራት ደግሞ ዘመኑ የሚጠይቀው ሥራ ነው። ለዚህ በዘርፉ የተሰማሩ ዲዛይነሮች የኢትዮጵያን ልብሶች ባሕላዊ ይዘታቸውን ሳይለቁ በተለያዩ አማራጮች በማዘጋጀት በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳድረው ተመራጭ ሆኖ እንዲታዩ ለማስቻል ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ።

ከአልባሳቱ ባለፈም በአገሪቱ የሚገኙ የሀበሻ ልብስ ዲዛይነሮችም እንዲሁ ጎልተው እየወጡ ይገኛሉ። ከእነዚህ ዲዛይነሮች መካካል ‹የአብ ጥበብ› የተሰኘ ድርጅት መስራች ዲዛይነር የኔነሽ አቦነህ አንዱ ናት።

ዲዛይነር የኔነሽ፤ ወደዚህ ሙያ ከገባች 14 ዓመታት ገደማ ተቆጥሯል። በቀለም የተነከረ የሀበሻ ልብስ በመስራት ይበልጥ ትታወቃለች። የምትሰራቸውን የሀበሻ ልብሶች በቀለም በመንከር በተለያየ አማራጭ እየሰራች ለገበያ ታቀርባለች። ከዚህም በተጨማሪ የሀበሻ ቀሚሶችን፣ ቶፖችን እንዲሁም ለሴት እና ለወንድ የሚሆኑ ልብሶችን ትሰራለች። እንዲሁም ለሕጻናት የሚሆኑ የሀበሻ ልብሶችን በተለያየ ዲዛይንና አይነት ትስራለች። አሁን ላይ ደግሞ ተደራሽነትዋን በማስፋት የአልጋ ልብስ፣ የጠረጴዛ ልብሶች እና እንደ ሶፍት የሚያገለግሉ ልብሶች በተለያየ ዲዛይን



ንክር የሀበሻ ቀሚስ

በመስራት ለገበያ እያቀረበች ትገኛለች።

ዲዛይነር የኔነሽ የዲዛይኒንግ ሙያ ገና ተማሪ ሳለች ጀምሮ ውስጧ ተዳፍኖ የኖረ መሆኑን ትናገራለች። ወደ ሙያ ለመግባት መጀመሪያ የስፌት ሙያ ተምራ እንደነበረ በማስታወስ፤ ቀጥላም ያላትን እውቀት በመጠቀም የዲዛይኒንግ ሙያ በመማር ሙያዋን እያሳደገች መጥታለች።

‹‹በተለይ ለቀለማት ጥምረት ትኩረት ሰጥቼ በተመስጦ መስራት በመቻሌ የቀለማቱ ጥምረትና የምሰራቸው ዲዛይኖች በብዙዎች ሰዎች ዘንድ ተወዳጅ ናቸው›› የምትለው ዲዛይነሯ፤ የሀበሻ ልብሶች ዕለት ተዕለት እንደ ዘወትር ልብስ እንዲለበሱ በማሰብ ቀለል አድርጋ እንደምትሰራ ትናገራለች።

በተለይ በተለያዩ ቀለማት በመንከር የምታቀርባቸው ንክር የሀበሻ ልብሶች ተመራጭና ተፈላጊ ናቸው። ንክር ልብሶቹ ቀለል ያሉና በጣም የሚመቹ እንደሆኑም ነው የምትገልጸው። ለባሾችም ‹‹ነጭ የሆነው የሀበሻ ልብስ ያወፍረናል›› ብለው ስለሚያስቡ በቀለም የተነከረው በአማረ ዲዛይን የተሰራውን ልብስ መልበስ የሚመርጡ መሆኑን ዲዛይነሯ አንስታለች››።

በቀለም የተነከሩ የሀበሻ ልብሶች ከጊዜ ወደ ጊዜ ተፈላጊነታቸው እየጨመረ የመጣ ሲሆን፤ በተለይ በበዓላት፣ በሰርግ እና በተለያዩ ፕሮግራሞች ላይ ለየት ብለው ደምቀው ለመታየት የሚፈልጉ ሰዎች ምርጫዎች ነው። በአዘቦትም ቀንም እንዲሁም እየተለመዱና በተለያዩ ቦታዎች እንደማንኛውም ልብስ ይለበሳሉ። ልብሶቹ በአገር ውስጥ ገበያም ሆነ በተለያየ መልኩ ውጭ አገር ድረስ የሚሄዱ ሲሆን በተለይ ከውጭ አገር የሚመጡና ገዝተው የሚሄዱ ሰዎች በክረምት ለመልበስ እንደሚመርጧቸው ዲዛይነር የኔነሽ ትገልጻለች።

ለምትሰራቸው ንክር ልብሶች የምትጠቀመው ከለር ለልብሱ የሚስማማው አይነት ስለሆነ የማይለቁ እና እንደነበሩ የሚቆዩ ናቸው የምትለው ዲዛይነሯ፤ ‹‹ንክር ልብስ ሲባል እኔ የምሰራው ንክር ልብስ የሚለቅ አይደለም ለዚህም፤ ስምንት እና ዘጠኝ ዓመታት ያህል የለበስኳቸው ልብሶች እንደ አዲስ መታየታቸው ምስክር ነው›› በማለት ትገልጻለች። ለምትሰራቸው ልብስ የሚስማማ ቀለም የምትጠቀም በመሆኑንም ንክር ልብስ የሚፈልጉ ብዙ ሰዎች እሷን ምርጫ አድርገው እንደሚጎበኟት ትናገራለች።

የልብሱን ባሕላዊ ይዘታ ሳይለቁ በተለያየ መልክና ዘመኑን በሚመጥን ደረጃ ዲዛይን ካደረገች በኋላ ወደ ቀለም መንከር ሥራ እንደምትገባ የምትናገረው ዲዛይነሯ፤ ቀለሙ መንከር የምትፈልገው ልብስ በምትፈልገው የቀለም አይነት በመንከር ውብና ማራኪ ሆኖ በለባሾች ዘንድ የሚወደድ እንዲሆን ጥረት እንደምታደርግ ትገልጻለች።

ዲዛይነር የኔነሽ፤ ምርቶቿ ለማስተዋወቅ የተለያዩ ድረገጾችና የማኅበራዊ ሚዲያ አማራጮች (እንደ ፌስ ቡክ፣ ኢንስትግራም እና ቲክቶክ) በመሳሳሉ በማስተዋወቅ ለገበያ እያቀረበች ትገኛለች። አልፎ አልፎም ቢሆን በመጽሔቶች (ኢትዮጵያን ሪቪዩ እና ሪፖርት የተሰኙ መጽሔቶች) ሥራዎቿ ማስተዋወቋን ትገልጻለች።

የምትሰራቸው ልብሶች ጥራታቸውን የጠበቁና በኤክስፖርት ደረጃ ያሉ ሲሆን፤ ወደ ውጭ ለመላክ የገበያ ትስስር ለመፍጠር ጥረት እያደረገች መሆኑን ገልጻ፤ ምርቶቿ ዓለም አቀፍ ገበያን እንዲቀላቀሉ ጥረት ማድረጓን ነው ያመላከተችው።

‹‹የባሕላዊ አልባሳት ያለንን ቱባ ባሕል በአልባሳቶቻችን በመግለጽ ለዓለም የምናስተዋውቅበት አንዱ መንገድ በመሆኑ በደንብ ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራበት ይገባል›› የምትለው ዲዛይነሯ፤ ከዚህ ባሻገር ዘርፉ ለአገር ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪን ማምጣትና ለብዙ ሰዎች የስራ እድል መፍጠር የሚችል በመሆኑ ተገቢው ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ባይ ናት።

አሁን ላይ እነዚህን ምርቶች ለማምረት ለአሥራ አንድ ዜጎች ቋሚ የሥራ እድል የፈጠረች ሲሆን፤ የሸማኔዎችና የጥልፍ ሥራ ለሚሰሩ ለብዙ ባለሙያዎች ጊዜያዊ የሥራ እድል መፍጠሯንም ገልጻለች።

ባሕላዊ አልባሳት ዋጋ በአንድ ቦታ የሚቀመጥ አይደለም፤ እንደጊዜው የጥሬ እቃ አቅርቦት ሁኔታ መሠረት በየጊዜው እየጨመረ የሚመጣ ነው የምትለው ዲዛይነሯ፤ ሆኖም ግን የምትሰራቸውን ልብሶች ኅብረተሰቡ በየደረጃ ሸምቶ ሊለብሰው በሚችል መልኩ በተመጣጣኝ ዋጋ ለገበያ እያቀረበች መሆኑን ነው የገለጸችው።

የአገር ባህል አልባሳት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪና ተመራጭ እንዲሆኑ በባለሙያው ሆነ በሚመለከታቸው አካላት መስራት ያለበት ብዙ የቤት ሥራዎች እንዳሉ የምትናገረው ዲዛይነሯ፤ ባለሙያው ሙያ የሚጠይቀውን ሥነምግባር ከግምት ውስጥ በማስገባት በትክክል ጥራታቸውን የጠበቁ የሀገሩን ባሕል ሊገልጹ የሚችሉ ልብሶቹን ሰርቶ ለገበያ ማቅረብ እንደሚጠበቅበት ትገልጻለች። የሚመለከታቸው አካላት እንዲሁ ለዘርፉ ተገቢው ትኩረት በመስጠት በዘርፉ የሚነሱ ችግሮች የሚቀረፉበት መንገድ ማመቻቸት ይኖርባቸዋል። ይህ ከሆነና በዚህ መንገድ መጓዝ ከቻልን በዓለም አቀፍ ደረጃ ጎልቶ የሚታዩ ሥራዎች ይዞ መምጣት ይቻላል ስትል ምክረ ሀሳብ ትለግሳለች።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ሕጉ ለማን ለምን ?

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

መሽቶ በነጋ ቁጥር በመኪኖች አጀብ የሚጨናነቀው መንገድ ዛሬም እንደሌላው ቀን ብሶበታል። ግዜው እየመሸ ነው። በዚህ ሰዓት ከሥራ ወደ መኖሪያው የሚመለሰው ሰራተኛ ይበረክታል። ለጉዳይ ወጣ ያለውም ቢሆን ‹‹ዞሮ ከቤት›› እንዲሉ የመመለሻ ሰዓቱ ይህ ግዜ ነው።

በተወሰኑ ቦታዎች ለአውቶቡሶችና ለሰራተኞች ሰርቪስ ተብለው የተፈቀዱ መንገዶች በዚህ ሰዓት የተሻለ ጉዞ አላቸው። አብዛኛውን ግዜ የትራፊክ ፍሰቱ ለእነሱ መልካም ይሆናል። ብዙዎች የሚቸገሩበት የመጨናነቁ ጣጣ እምብዛም አያገኛቸውም። ይህ የአሰራር ልማድ በሁሉም የከተማው መንገዶች ባይሆንም በተመረጡ አካባቢዎች ተግባራዊ መሆን ከያዘ ቆይቷል።

እንዲህ መሆኑ ከፍ ከሚሉት መኪኖች ግርጌ የሚጓዙ አነስተኛ ተሽከርካርካሪዎች ለሕግ ተገዢ እንዲሆኑ አስችሏል። በዚህ ሰዓት መንገድ ለመሻማት ከመሀል አፈንግጠው ከዳርኛው መንገድ የሚገቡ ቢኖሩ መብት የተሰጣቸው ታላላቆቹ መኪኖች ‹‹በጄ›› አይሏቸውም። እነሱ እንኳን ቢያስገቧቸው ትራፊኮችና የመንገድ ትራንስፖርት ባለሙያዎች አይለቋቸውም። ከተያዙ ደግሞ ‹‹ሕግ ጥሰዋል›› በሚል ቅጣት ያገኛቸዋል ።

በጣም አስገራሚው ጉዳይ ግን በነዚህ መንገዶች ላይ የሚስተዋለው ሕግን የመጣስ እውነት ነው። ሕጉ የሚጣሰው ደግሞ በመንገዱ ላይ በሚዘዋወሩ መኪኖች እንዳይመስላችሁ። በነዚህ የተመረጡ መንገዶች ላይ ሕጋዊ ታርጋ ያልተለጠፈባቸው፣ ትራፊኮችም ሆኑ የመንገዱ ባለሚሎች ያላስተዋሏቸው ሕግን ተጋፊዎች አሉ።

ሕጉን ጥሰው መንገዱን ከሚጋፉት መሀል ዋንኞቹ ጋሪ ሙሉ ሙዝና ፓፓዬ ቆልለው ግዙን የሚሉ ነጋዴዎች ናቸው። እነዚህ ሰዎች ሁሌም ንግዳቸውን የሚያካሂዱት በእግረኛው መንገድ ላይ አይደለም። ከዋናው ጠርዝ አለፍ ብለው ወደ መኪናው መንገድ ገባ ብለው እንጂ።

አስገራሚው ጉዳይ መንገዱን ተጋፍተው ለጉዞ አስጊ የሚሆኑትን ሕግ አልቦ ነጋዴዎች ልብ ብሎ ‹‹በሕግ አምላክ›› የሚላቸው አለመኖሩ ነው። እንደውም አብዛኞች ሾፌሮች ስራቸውን እንደ ግዴታ የቆጠሩት ይመስላል። መንገዱን እንዲለቁላቸው ከማስገደድ ይልቅ በጥንቃቄ እየተካኩ በጎናቸው ማለፍን ልምድ አድርገውታል።

በየቀኑ ደረሰኝ ይዘው የሚቀጣን ሾፌርና መኪናውን ለመያዝ የሚያንጋጥጡ ትራፊኮችና የመንገድ ባለሙያዎችም ስለ እነዚህ ወገኖች ግድ የሚላቸው አይመስልም። መሀል መንገድ ገብተው ከመኪኖች ሲጋፉ፣ የእጃቸውን ለመሸጥ ሲራወጡ እያዩ ዝምታን መርጠዋል።

በአጋጣሚ አደጋ ቢደርስ ሁሌም እንደሚሆነው ተጠያቂው አንድ ወገን ብቻ ይሆናል። እንዲህ ማድረጉ ደግሞ ለማንም ለምንም አይበጅም። እንደ እኔ ሀሳብ ሕግ የሚወጣው ለሁሉም በእኩል ሊሆን ይገባል። አንዱ ወገን ብቻውን በሚፈጥረው ችግር ብዙሀንን ለሚጎዳ አደጋ መጋለጡ አይቀሬ ነውና።

ዛሬ ከተማችን በለውጥ ጉዞ ላይ ነች። በየግዜው አዳዲስ ግንባታዎች ይከወኑባታል። ዘመኑን የዋጁ ድንቅ ሕንፃዎች ይገነቡባታል። እንዲህ መሆኑ ታላቅ ለውጥ ነው። አሮጌው በአዲስ ሲተካ ዘመናዊነት ጎልቶ ሲታይ እሰዬው ያሰኛል። አንዳንዴ ደግሞ ከግንባታዎች ተያይዞ የሚታዩ ችግሮች ጉዳታቸው ይስተዋላል። ካለመጠንቀቅ በሚከሰቱ አደጋዎች ጭምር በርካቶችን ሰለባ ይሆናሉ።

እርግጥ ነው ጥቂት የማይባሉ የሕንጻ አሰሪዎች ግንባታዎቻቸው ላይ ይጠነቀቃሉ። ለሌሎች ደህንነትም ያስባሉ። ይህ እውነታ በርካቶችን ይታደጋልና ምስጋናውን ሊወስዱ ይገባል። የበጎ አርአያነታቸው ጠቀሜታ ለብዙሀኑ ነውና።

አብዛኞቹ ግን ፎቆቻቸው ከፍ ባሉ ቁጥር ስጋታቸው በእኩል ይጨምራል። ብዙ ግዜ ለመንገደኞች፣ ለአካባቢው ነዋሪዎችና በዙሪያቸው ላሉ ቤቶች ሲጨነቁ አይስተዋሉም። እንዲህ አይነቶቹ፣ አሰሪዎች በሕንፃዎቻቸው ላይ የደህንነት መጠበቂያ መጠቀምን አያውቁትም። በግልጽ እንደሚስተዋለው የግንባታ ግብአቶቻቸው ለበርካቶች ደህንነት ስጋት ናቸው።

ልብ ብላችሁ ከሆነ በርካቶቹ የከተማችን ሕንጻዎች ግንባታ ለደህንነት ስጋት የተጋለጠ ነው። በአጠገባቸው የሚያልፍ እግረኛ ለአሸዋ፣ ሲሚንቶው፣ ለእንጨትና ሚስማሩ እንደተጋለጠ ይውላል። ከፍተኛ ክብደት ያላቸው ብረቶች፣ ብሎኬቶችና የሴራሚክ ውጤቶች ከላይ ታች የሚመላለሱት በተለየ ጥንቃቄ ተሸፍነው አይደለም።

እንደውም አንዳንዴ በወጉ ያልተገጠሙና ንፋስ ያገኛቸው መስታወቶች ድንገት ወድቀው ይከሰከሳሉ። አወዳደቃቸው ደግሞ በራሳቸው ይዞታ ስር የማይሆንበት አጋጣሚ ብዙ ነው። ከእነሱ አልፎ በአካባቢው በሚገኙ ሰዎች ላይ የማረፍ ዕድሉ ሊሰፋ ይችላል።

የእነዚህ ሕንጻዎች ግንባታ በገፋ ቁጥር እነሱን የሚፈሩ፣ በሩቁ አይተው የሚሸሹ ይበዛሉ። ከአሁን አሁን ‹‹በላያችን አንዳች ነገር ወደቀብን›› የሚሉቱ እርምጃቸው ሁሉ በመሳቀቅ ይሆናል። ከመንገደኞች ባለፈ በአካባቢያቸው የሚቆሙ መኪኖችም ዋስትና የላቸውም።

አልፎ አልፎ እንደሚታየው በእንዲህ መሰል ስፍራዎች መኪኖች እንዳይቆሙ ማስጠንቀቂያና ቁጣ መሰል ጽሁፎች ይለጠፋሉ። ይህ ብቻውን ግን በቂ የሚባል አይደለም። ማሳሰቢያውን በወጉ እንየው ከተባለ የአንድ ወገንን መብት አክብሮ የሌላውን የሚጋፉ ይዘት ያለው ይመስላል።

በአጋጣሚ ጽሁፉን ሳያስተውል ቀርቶ ችግሩ የሚገጥመው ባለመኪና ቢኖር ስለምን ቆምክ ሊባል አይገባም። ማሳሰቢያው በሆነ አካል በቁራጭ ወረቀት ስለተለጠፈ ብቻ ሕጋዊ ነው ማለት አይደለም። አደጋ አድራሹንም ቢሆን ከተጠያቂነት አያስጥልም።

ከጥቂት ጊዚያት ወዲህ መንገድን በሰፋፊ ድንኳኖች ዘግቶ ድግስና ጭፈራ ማዘጋጀት እየተለመደ ሄዷል። ይህ አይነቱ ጉዳይ በተለይ ለሆቴሎችና ለመጠጥ ግሮሰሪዎች ምርቃት በሚል ዓላማ የሚካሄድ ነው። ይህ ቆይታውን ከአንድ ቀን በላይ የሚያደርገው የጎዳና ላይ ግርዶሽ እግረኛውን ከመንገድ የሚያስወጣና የብዙሀንን መብት የሚጋፋ መሆኑ ይታወቃል።

በዚህ ገጽ ላይ የተቀመጡትን ጥቂት ችግሮች ጨምሮ ሌሎችንም ፈታኝ ጉዳዮች መዘርዘርና ማንሳት ይቻላል። ለእንዲህ አይነቶቹ ያልተገቡ ተግባራት የተቀመጠ ደንብና መመሪያ ቢኖር ደግሞ ሕጉን ተግባራዊ ለማድረግ ያግዛል። ይህን እውነታ ለሚመለከታቸው አድርሶም የአደጋ ስጋትን ይቀንሳል።

የመንገድ ላይ የሙዝ ጋሪዎችን ጨምሮ ብዙ ግዜ ትናንሽ የሚመስሉን ጉዳዮች ጎልተው የሚታዩት ችግሩ በተከሰተ ግዜ ነው። ከአደጋዎች በኋላ ደምቀው የሚሰሙ ዘገባዎችም የአንድ ሰሞን ርዕስ ከመሆን የዘለለ ፋይዳ የላቸውም። እንዲህ አይነቶቹን ችግሮች ስናነሳ ሁሌም ለምንና እንዴት የሚል ጠያቂ ባለመኖሩ ችግሮች ሳይቀረፉ መቀጠላቸውን ልብ ልንል ይገባል።

ከዚሁ የግንባታ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የሚከሰት የመንገድ ላይ ችግርም ፈተናው ተመሳሳይ ነው። ለግንባታቸው ሲሉ መሀል ጎዳናውን ዘግተው እግረኛውን ከመንገዱ ስለሚያስወጡ አካላት አንዳች የሚባል የለም። በዚሁ ሰበብ ችግር ሲያጋጥም ግን እንደተለመደው ወሬው ተናፍሶ የሕጉ ጉዳይ ይዘነጋል።

እነዚህና ሌሎች ጥቃቅን መሰል ጉዳዮች ሁሌም የችግራቸው መዘዝ ከፍ ብሎ ይታያል። በየዕለቱ አብረውን ያሉ እንቅፋቶች ቢሆኑም ግን ልብ ብለን ትኩረት ስንሰጣቸው አይስተዋልም። ከጉዳዮቹ አሳሳቢነት አኳያ በሕጉ በኩል በመመሪያ የታሰረ አፈጻጸም ስለሌላቸውም እንደ ችግር ተይዘው መፍትሄ ሲበጅላቸው አይስተዋልም።

ለእይታና ለጉዳዩ ሚዛንነት ጥቂት የሚመስሉን፤ ችግር ሆነው ሲከሰቱ ግን ጉዳታቸው ጎልቶ የሚታይ እንከኖች ከቁጥር በላይ ናቸው። ጉዳዮቹን በሕግና መመሪያ አስሮ መፍትሄ መሻት ከተቻለ ግን ውጤቱን መልካም ማድረግ ይቻላል። ‹‹ትንሽ ምላጭ አገር ትላጭ›› እንዲሉ የችግር ትንሽ የለውም። በሕግና መመሪያ ማሰሩ ደግሞ ጥቅም እንጂ ጉዳት የለውምና ልብ ሊባል ይገባል።

## ነፃ ሃሳብ

# ትውልድን የሚያነቃ ትርክት ለመገንባት

### ታሪኩ ዘለቀ

እኤአ የካቲት 1926 በአገረ አምሪካ በጥቁሮች ሕይወትና ታሪክ ጥናት ማኅበር አማካኝነት የካቲት የጥቁሮች ወር (Black History Month) ተብሎ እንዲጠራ ተወሰነ፡፡ ይህ ውሳኔ በአሜሪካና በካናዳ መንግስት ወዲያው እውቅና ተቸረው። በቅርቡ ደግሞ በአየርላንድና በዩናይትድ ኪንግደም ተቀባይነት አገኘ። አሜሪካና ካናዳ በየካቲት ወር ሲያከብሩት ቀሪዎቹ ሁለቱ አገራት ደግሞ በሕዳር ወር አስበውት ያልፋሉ።

በዋናነት አፍሪካ አሜሪካውያንና ጥቁር ዳያስፖራዎች የካቲት ወርን ምርጫቸው አድርገዋል። ወሩ ለዚህ ክብር የተመረጠበት ምክንያት የጥቁሮች ነፃነት መሰረት የነበሩት 16ኛው የአሜሪካ ፕሬዚደንት አብርሃም ሊንከንና አፍሪካ አሜሪካዊው የሰብዓዊ መብት ተሟጋችና የነፃነት አርበኛ ፍሬድሪክ ዳግላስ የተወለዱበት በመሆኑ ነው፡፡ ቀኑ ላለፉት 50 ዓመታት በአፍሪካ አሜሪካውያን ዘንድ ሰፊ ተቀባይነት እያገኘ መምጣቱ ይነገራል፡፡

ወርሃ የካቲት ከዚህም ሌላ ታላቅ ቁምነገርም ይዟል። ኢትዮጵያውያን በታላቅ የድል ስሜት የሚያስቡት ነው። በጥቁር ላይ ይደርስ የነበረው የባርነት ቀንበር የተሰበረበት የነፃነት ጮራ የፈነጠቀበት፣ እና የትግል አድማሱ እንዲሰፋ አርዓያ የሆነው የዓድዋ ድል በኢትዮጵያውያን አርበኞች የተመዘገበበት ነው፡፡

የዓድዋ ድል የነፃነት ጎህ ፈንጣቂ ነው፡፡ ይህ ታላቅ ድል በዚሁ ወር የካቲት 23 ቀን ነው የተገኘው። በዓድዋ ተራሮች በደምና በአጥንት የሰውን አስተሳሰብ እጥፋት የቀየሩ አያቶቻችን የተጋድሎ ታሪክ ለመላው ጥቁር ሕዝብ የነጻነት ችቦ የሆነበት ነው፡፡ ለዚህም ነው ዓድዋና የፓን-አፍሪካኒዝም ላይነጣጠሉ የተጋመዱት፡፡

የዓድዋ ጀግኖች ቀኝ ገዢዎች ላይ የተቀናጁት ድልም ከአትላንቲክ ማዶ ድረስ የነዘረ የነጭና ጥቁር ይሉት የቆዳ ቀለም ድልድልን የሰበረ፣ በሰው ልጆች ታሪክ ፍትህና እኩልነትን ያነበረ፤ ሁሌም መቼም የምንኮራበት የጋራ የታሪክ ገፃችን ነው፡፡

ዶክተር ዊሊየም ኤድዋርድ ከፓን አፍሪካ ንቅናቄ ፋና ወጊ መሪዎች መካከል አንዱ ናቸው፡፡ የዓድዋን ድል ሲገልጹት «ዓድዋ በቀኝ ገዢዎች ትግል አይበገሬ መንፈስ ላላቸው እንዲሁም ለነፃነታቸው ፋና ወጊ ለሆኑ አፍሪካዊያን ሕዝቦች ምስክርነት የቆመ ድል ነው» በማለት ነበር፡፡ እነ ማርክስ ጋርቬ ፣ ዶክተር ክዋሚ ኒክሩማ፣ ኔልሰን ማንዴላ፣ ፓትሪክ ሉሙምባ ስለ ዓድዋ ድል የነፃነት ቀንዲልነት ደጋግመው መስክረዋል።

የጥቁሮች ወር ተብሎ የሚታወቀው ወርሃ የካቲት የነፃነት ቀንዲል ከሆነው የዓድዋ ድል ጋር የታሪክ ግጥምጥሞሽ ፈጥሯል፡፡ ጥቁሮች ለነፃነታቸው ያደርጉት የነበረውና አንድ ጊዜ ሞቅ ሌላ ጊዜ ቀዝቀዝ ይል የነበረው ሂደቱ የተቀጣጠለው በዓድዋ ድል ምክንያት ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን አርበኞች ወራሪውን የጣሊያን ሰራዊት ድል በመምታት ለመላው ጥቁር ሕዝቦች የነጻነት ችቦ ለኩሰዋል፡፡ ይህንን ተከትሎ አፍሪካውያን ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ በወሰደው የነጻነት የተጋድሏቸው በኢትዮጵያኒዝም ንቅናቄ ገዢዎቻቸውን አንበርክከዋል፡፡ የሰንደቋን ቀለማትም የአሸናፊነት መገለጫ አድርገው ወስደዋል፡፡

በአፍሪካ ምድር የምትገኝ ኢትዮጵያ የተሰኘች ሀገር በዘመኑ የሰለጠነና እስካፍንጫው የታጠቀ ወራሪ በጦርና ጋሻ ድባቅ መምታት ችላለች። ድሉ የሰው ልጆች ከቀለም ልዩነት ውጪ የሚለያቸውና አንዱን የበታች አንዱን የበላይ የሚያደርግ ምንም አይነት ኃይል እንደሌለ ማስረዳት ችሏል። የሰው ልጆችን እኩልነት አስርጿል። የጥቁር ሕዝቦችን ስነልቦና እንዲነቃቃ እርሾ ነበር፡፡

አዲስ አበባም ዓድዋን በግዙፍ አሻራ ሀገሪቱ እምብርት ላይ አኑራ፣ በፓን አፍሪካኒዝም እሳቤ ጠንካራዋን አህጉር ለመፍጠር የሚታትሩ መሪዎቿ በመዲናቸው ተሰባስበው መምከሪያ ሆናለች፡፡ ይህ ታሪካዊ ግጥምጥሞሽ አንድም ለጉዳዩ የሰጠነው ክብር የሚያሳይ ሁለትም የነፃነት ቀንዲል የተከፈለበት ዋጋን ግልፅ የሚያደርግ ነው፡፡

የአፍሪካ መዲናነቱ እንዲሁ ባጋጣሚ የተገኘ በረከት ሳይሆን ከወሳኝ የታሪክ ውለታዎች ጋር የሚተሳሰር መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ለመላው አፍሪካውያን የጭቆናን ቀንበር አሽቀንጥረው ይጥሉ ዘንድም የብርታት ትጥቃቸው፣ የአሸናፊነት መንፈስ መገኛ ማዕከል በመሆናችን ምክንያት የተገኘ መሆኑን ልብ ማለት ይገባል፡፡

ወርሃ የካቲት የዓድዋ ድልና የፓን አፍሪካኒዝም በአንድነት በሕብረ ቀለማት የደመቁበት እንደመሆኑ እኛ ኢትዮጵያውያን ወቅታዊ ለሆነውና ልዩነታችንን ለማስፋት ለሚነዙ የሀሰት ትርክቶች ማረቂያና በጋራ ለመሰባሰብም ጥላ እንዲሆነን ልንሰራበት ይገባል፡ ፡ ወሩ በዓለም ጥግ ያሉ ጥቁሮች ሁሉ አንገታቸውን ቀና አድርገው ለመብታቸው የሚከራከሩበት የታሪክ እጥፋት የተፈፀመበት ወቅት ነው፡፡ እንደዚህ አይነቱ የታሪክ የከፍታ ቦታ ላይ ባለቤት ሆኖ ለመዝለቅ ደግሞ ታሪክን መረዳት ያስፈልጋል፡፡

የ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ታዋቂው እንግሊዛዊው ደራሲ ጆርጅ ኦርዌል «ታሪክ በዘመን ጀግኖች የሚሰራ አሻራው ግን ትውልዶችን ተሻግሮ የሚዘከር ገድል ነው» ብሏል፡፡ ይህ ተግባር ደግሞ በዘመን ጅረት ውስጥ ትውልድ የሚጋደልበት ወይም የመሰባሰቢያ ጥላ ሊሆን ይችላል፡፡ እዚህ ላይ የታሪክ ባለሙያዎች ታሪክና ትርክትን የሁለቱ ሚዛን አድርገው ይመለከቱታል፡፡

የታሪክ ተመራማሪዎች እንደሚሉት በተለይ በኛ ሀገር ታሪክና ፖለቲካ ሚናቸው ተደበላልቋል፡፡ እናም ፖለቲከኛው እንደዜጋ የሀገሩ ታሪክ ጉዳዩ ቢሆንም የፖለቲካው መታገያው አድርጎ እውነትን መሻሩ የሂደቱ ፈተና ሆኗል፡፡ በባለሙያዎችና በፖለቲከኞች ሀሳብ ምክንያት የሚነገሩ ትርክቶች ማኅበረሰቡም ሰለባ እየሆነ ነው፡፡ ባለሙያዎች የሚገባቸውን ያክል ወደፊት ገፍተው እውነትን ለመናገር ስለእውነት ቆመው ለእውነት ለማለፍ ዝግጁ ሲሆኑ አይታዩም፡፡

ባለሙያዎች ባገኙት አጋጣሚ የተለያዩ ምርምሮችን በመስራት ታሪክ ለዴሞክራሲያዊ ሀገረ መንግስት ግንባታ፣ ታሪክ ለብሔራዊ ውይይትና ለሀገራዊ ሰላም ያለውን አስተዋፅኦ ሙያዊ በሆነ መልክ የምርምር ስራዎችን ወደ አደባባይ በማቅረብ ሕዝብን ማስተማር ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ኢትዮጵያውያን ለጥቁር ሕዝቦች ያበረከቱት የነፃነት ተጋድሎ እየተዘከረ ያልፋል፡፡ ዛሬ ላይ ግን የኢትዮጵያውያን የአብሮነት ታሪክ የተነገረበት መንገድ የልዩነት ሆኖ ወንድም ከወንድሙ ተጣልቷል፤ ተጋድሏል፡፡ ትርክት ለዘመናት የቆየውን አብሮነት አናግቷል፣ አሻክሯል ለዘመናት ተገንብቶ የቆየውን ሰላም አደፍርሷል፡፡ የልዩነት ትርክት ራሳቸውን ከሀገር አብልጠው ለሚወዱ፣ አንድነትን ለማይፈልጉ በአብሮነት ውስጥ ሳይሆን በልዩነት ለሚያተርፉ ጠቅሟል፡፡

አሁን እየታየ ያለው የኢትዮጵያውያን የልዩነት መንገድ ያለንን እንዳናውቅ አድርጎ ሰፊውን የጋራ መንገድ በከበባ አጥረን በቀጭኗ መንገድ እንድንጋፋ አድርጎናል፡፡ በሀይማኖት፣ በባህል፣ በቋንቋ ተጋመድን የተፈጠርንና ለበርካታ ሺህ ዓመታት አብረን እየኖርን በመሆናችን እንጂ የተሄደበት ትርክት ሊያቀራርብ አብሮ ሊያኖር የሚያስችል አልነበረም፡፡

ባለፉት ዓመታት ጥላሸት ተቀብቶ የትውልዱ መጋደያ የሆነው የኢትዮጵያ ታሪክ ቅድመ አያቶቻችን የጋራ ችግሮቻቸውን በጋራ በመፍታት የጋራ ጠላት ሲመጣ ደግሞ በጋራ በመነሳት ዘመናዊ ኢትዮጵያን ዓድዋ ላይ አስረክበውናል፡፡ በኋላ የመጣው ትውልድ ግን በሆነው ባልሆነው እየተሻኮተ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ስናረክስ ይታያል፡፡

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዓብይ አሕመድ ከሰሞኑ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባደረጉት ንግግር «በትላንት ጉዳይ እየተባላን ነገ እያመለጠን ነው» ያሉ ሲሆን ነገን ለመያዝ ደግሞ ዛሬ ብቸኛ የመቆጣጠሪያ መሳሪያችን ስለመሆኑ ተናግረዋል፡ ፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ «ሰው ከትላንት ተምሮ ዛሬ ሰርቶ ነገን ማነፅ ሲገባው ዛሬ ላይ ሆኖ ትላንትናን እየተፋጀ ነገን እያጣን ነው፡፡ የተዘጋጁ ብቻ የሚወርሱ ስለሆነ በደምብ ካልተዘጋጀን ጥፋት ሊያመጣብን ይችላል፡፡ ለዚህም የሚያሰባስብ ትርክት ያስፈልጋል፡፡ ልክ እንደ ዓድዋ» በማለት መፍትሄውን አስቀምጠዋል፡፡

ታሪክ ትላንት የተፈፀመ ቢሆንም አሻራው ግን እስከ ነገ ይሻገራል፡፡ እናም ከዚህ ተምሮ ጠንክሮ መቆምን ታሪካቸውና መስፈንጠሪያቸው ካደረጉቱ አገራት እንማር ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያሳስባሉ፡፡ በሕንድ ሀገር እርስበርስ ሊደማመጡ የማይችሉ ከመቶ ሃያ በላይ ቋንቋዎች አሉ፡፡ ይሄ ልዩነት ለዘመናት ቢያስቸግራቸውም በመመካከርና በጥበብ አልፈውት አሁን ሰልጥነው አድገው በዓለም ላይ 5ኛውን ኢኮኖሚ መገንባት ችለዋል፡፡ መሰል ልዩነቶችን ሌሎች መባያ አድርገውታል፡፡ ተሞክሮውን ወስደን የሚያለያየንን ነገር ይዘን ለጋራ ሀገር ልንተጋ ይገባል እንጂ ልንባላ አይገባም፡፡

ከታሪክ ብዙ ልንማር እንጂ የመለያየት ሽንቁር ልንፈጥር አይገባም። እኛ ልንማርባቸው የምንችላቸው በርካታ ታሪኮች ደግሞ አሉን። አንድነታችንን ለማጠንከር የሚረዱ ታሪኮችን ሌሎች አገሮች ጋር ሄደን ሳይሆን እዚሁ ደጃችን ላይ ማግኘት እንችላለን። ብዙ ዶሴም ማገላበጥ አይጠበቅብንም። የየካቲት ወርን ብቻ ብንመዝ አስደናቂ ታሪኮችና ግጥምጥሞሽን ያመላክተናል።

በእብሪት ተወጥሮ ከ700 ኪሎ ሜትር በላይ የሀገራችንን ድንበር ዘልቆ የገባው ዚያድባሬ በ66ቱ አብዮት የተከፋፈለውን ሰራዊት መዳከም ተገን አድርጎ ነበር፡፡ የየካቲቱ አብዮት የፈጠረው መከፋፈልና የሽብር አዙሪት ሀገርን ቢያዳክምም ለሀገሩ ምንጊዜም ሟች ለሆነው ኢትዮጵያዊ ከያለበት ተጠራርቶ በዚች የካቲት ወር የካራማራን ድል አስመዝግቦ የምስራቁን ድንበር ለዘለቄታው አስከብሯል፡፡ ይህ ታሪክ በሉአላዊነታችን የማንደራደር፣ በአንድነታችን የማንቆምር መሆናችንን የሚያሳይ አጋጣሚ መሆኑን ልንዘነጋ አይገባም።

የየካቲት ገድል ብዙ ነው፡፡ ከእያንዳንዱ ድልና ሽንፈት ተምረን መወጣጫ ካላደረግነው ግን በየዓመቱ የአበባ ጉንጉን ከማስቀመጥ ያለፈ ፋይዳ አይኖረውም፡፡ ከድሎቻችን ጀርባ ሁሉ ሕብረታችንና መደማመጣችን ሲኖር ከሽንፈታችን ጀርባ ደግሞ ልዩነታችንና ክፍፍሎቻችን አሉ፡፡ ዛሬም ዓድዋና ካራማራ ልንደግምባቸው የሚገቡን ፀረ ድህነት ትግሎች አሉብንና እንደ ዓድዋውና እንደካራማራው ሁሉ በሕብረትና በአንድነት ልዘምትባቸው ይገባል፡፡

ዛሬም የልዩነት ሽንቁራችንን ለማስፋት የሚጥሩ ኃይሎች መኖራቸውን አንዘንጋ። ድክመታችንን ተገን አድርገው አጀንዳቸውን ለማሳካት በሚጣጣሩ ታሪካዊ ጠላቶች መከበባችንን አንዘንጋ። በድህነትና በስልጣኔ እጦት ተይዘዋል ብሎ የመጣውን ጣሊያንን አሳፍረው ከመለሱት አባት አርበኞች ልንማር ይገባል። በአንድነታችን እንደማንደራደር ሉአላዊነታችንን አሳልፈን እንደማንሰጥ የሚያሳየው የካራማራ ድል ማንቂያችን ይሁን።

ዛሬ ሌላ ዓድዋን የሚያክል ችግር ከፊት ለፊታችን አለ። ድህነትን ማሸነፍ የትውልዱ ሌላ ዓድዋ ነው። ለመልማት ወደብ ያስፈልገናል። ለማደግ አባይን ገንብተን ማጠናቀቅ እና ጥቅም ላይ ማዋል ያሻናል። ይህ እንዳይሆን ደግሞ ጠላቶቻችን ሽንቁሮቻችንን ተጠቅመው ሊያዳክሙን ይሻሉ።

የኢትዮጵያ የወደብ ጥያቄ ምንም ያህል ጤናማና ሕጋዊ ቢሆንም ዓለምን ሲያንጫጫ ተመልክተናል፡ ፡ ትንሿን የልማት እርምጃችንን በማጣጣል ሁሌም የተረጂነት ስሜት እንዲኖረን ሊሰሩብን የሚፈልጉ በርካቶች ናቸው፡፡ ይሄ የሚያሳየው የፖለቲካ ነፃነታችን ብቻውን ትርጉም እንደሌለውና የኢኮኖሚም ነፃነት ሊኖረን እንደሚገባ ነው፡፡ በመሆኑም ልዩነቶቻችንን በምክክር፣ በጠረጴዛ ዙሪያ በመፍታት አንድነታችንን ማጠናከር ይገባናል። መላው የጥቁር ሕዝብን ያስተሳሰረው የዓድዋ ድል የአንድነታችን መሰረት እንጂ ልዩነታችንን የሚያሰፋ ሽብልቅ አለመሆኑን እንገነዘብ። ለዚህ ነው እሩቅ ሳንሄድ የየካቲት ወር ታሪካዊ በረከቶቻችንን የሚጠበቅብን።

> **ኢትዮጵያውያን ለጥቁር ሕዝቦች ያበረከቱት የነፃነት ተጋድሎ እየተዘከረ ያልፋል፡፡ ዛሬ ላይ ግን የኢትዮጵያውያን የአብሮነት ታሪክ የተነገረበት መንገድ የልዩነት ሆኖ ወንድም ከወንድሙ ተጣልቷል፤ ተጋድሏል፡፡ ትርክት ለዘመናት የቆየውን አብሮነት አናግቷል፣ አሻክሯል ለዘመናት ተገንብቶ የቆየውን ሰላም አደፍርሷል፡፡ የልዩነት ትርክት ራሳቸውን ከሀገር አብልጠው ለሚወዱ፣ አንድነትን ለማይፈልጉ በአብሮነት ውስጥ ሳይሆን በልዩነት ለሚያተርፉ ጠቅሟል**

# ዓለም አቀፍ

## በሁቲ አማጺያን ጥቃት ከተፈጸመባቸው መርከቦች የመጀመሪያዋ ሰመጠች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የየመን ሁቲዎች አማጺያን በቀይ ባሕር በኩል በሚያቋርጡ መርከቦች ላይ ጥቃት መፈጸም ከመጀመሩ ከወራት በኋላ የመጀመሪያዋ ግዙፍ መርከብ ሰመጠች።

በብሪታኒያ የተመዘገበችው የጭነት መርከብ ማዳበሪያ ጭና በቀይ ባሕር በኩል ለማቋረጥ ስትሞክር ነበር ከሁለት ሳምንት በፊት በኤደን ባሕረ ሰላጤ ላይ በሁቲ ታጣቂዎች ሚሳኤል ተመትታ የቆመችው።

የየመን መንግሥት ባለሥልጣናት እንዳስታወቁት ሪቢይማር የተባለችው መርከብ ጥቃት ከተፈጸመባት በኋላ ውሃ ወደ ውስጧ እየገባ ለቀናት በባሕሩ ላይ ስትዋልል ቆይታ ሰምጣለች።

በኢራን የሚደገፉት ሁቲ አማጺያን ካለፈው ኅዳር አንስቶ በቀይ ባሕር የሚያቋርጡ መርከቦችን ዒላማ ማድረግ ከጀመሩ ወዲህ ይህች መርከብ ጥቃት ከተፈጸመባቸው መካከል በመስመጥ የመጀመሪያዋ ሆናለች።

የሰመጠችው መርከብ ማዳበሪያ ጭና እየተጓዘች ሳለ ነው በሁቲዎች ሚሳኤል የተመታችው። የመርከቧ መስመጥ በቀይ ባሕር ላይ "የተፈጥሮ አካባቢ ጉዳትን" የሚደቅን ነው ሲሉ ባለሙያዎች ተናግረዋል።

ሩቢይማር የተባለችው ይህች መርከብ በኤደን ባሕረ ሰላጤ በኩል ባብ ኤል መንደብ አቅራቢያ ሳለች ነው በየመን ሁቲ አማጺያን በተተኮሱ ሁለት ሚሳኤሎች የተመታችው።

ከአስር ቀናት በፊት የብሪታኒያ መንግሥት መርከቧ ላይ ጥቃት ከተፈጸመ በኋላ ወደ ውስጧ ውሃ እየሰረገ መሆኑን እና 24 የመርከቧ ሠራተኞችን ማትረፍ መቻሉን ገልጾ ነበር።

ከአንድ ሳምንት በፊት ቢቢሲ ያገኘው ምሥል ላይ



የተወሰነ የመርከቧ ክፍል በውሃ ተውጦ ቀሪው ክፍል በውሃ ላይ እየተንሳፈፈ ያሳይ ነበር።

የመርከቧ ባለቤቶች በወቅቱ መርከቧ ተጎትታ በአቅራቢያ ወደሚገኘው የጂቡቲ ወደብ እየተወሰደች መሆኗን፣ ነገር ግን ልትሰምጥ እንደምትችል አመልክተው ነበር።

መርከቧ በብሪታኒያ ተመዝግባ በአንድ የሊባኖስ ተቋም አማካይነት ስትንቀሳቀስ የቆየች ናት። ጥቃቱ በተፈጸመባት ጊዜም አሞኒየም ናይትሬት የተባለውን ማዳበሪያ ጭና እንደነበር ተነግሯል።

በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ እውቅና ያለው የየመን መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር አሕመድ ቢን ሙባረክ፣ የመርከቧን መስመጥ "አጋጥሞ የማያውቅ የአካባቢ አደጋ ነው" ሲሉ ገልጸውታል።

በዓለም ዙሪያ ላሉ የውሃ አካላት ደኅንነት የሚከራከረው የአካባቢ ጥበቃ ተከራካሪው ግሪን ፒስ በበኩሉ የአሞኒየም ናይትሬት ማዳበሪያው ወደ ባሕሩ መግባት "ከውሃ በታች ባለው ሥነ ምሕዳር ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖን ይፈጥራል" ብሏል።

ሁቲዎች በጋዛ ውስጥ ላሉ ፍልስጤማውያን ያላቸውን ድጋፍ ለማሳየት ካለፈው ኅዳር ጀምሮ በቀይ ባሕር እና በኤደን ባሕረ ሰላጤ በኩል በሚያቋርጡ ከእስራኤል ጋር ግንኙነት አላቸው ባሏቸው መርከቦች ላይ ጥቃት እየፈጸሙ ነው።

ለዚህም ምላሽ አሜሪካ እና ዩናይትድ ኪንግደም የመን ውስጥ በሚገኙ የሁቲ ይዞታዎች ላይ ተከታታይ የአየር ጥቃቶችን ፈጽመዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የዩናይትድ ኪንግደም የባሕር ላይ ንግድ ተቋም ቅዳሜ ዕለት እንዳሳወቀው፣ ከየመኗ ወደብ ሞካህ በስተምዕራብ አንዲት መርከብ ላይ ጥቃት እንደተፈጸመ ሪፖርት ደርሶታል።

ጨምሮም "የመርከቧ ሠራተኞች መልሕቋን እንድትጥል አድርገው በወታደራዊ ባለሥልጣናት ከመርከቧ እንዲወጡ ተደርገዋል" ብሏል።

የአሜሪካ ማዕከላዊ ዕዝ "እራስን ለመከላከል በተወሰደ እርምጃ" ከየመን በኩል በሁቲዎች ሊተኮስ ተዘጋጅቶ የነበረ ከምድር ወደ አየር የሚወነጨፍ ሚሳኤልን መምታቱን አሳውቋል።

ወታደራዊ ማዘዣው ሊወነጨፍ የነበረው ሚሳኤል በአሜሪካ አውሮፕላን ላይ አሳሳቢ ስጋትን ደቅኖ እንደነበር አመልክቷል።

የአማጺያኑ ጥቃት የዓለም የባሕር ላይ ንግድ 12 በመቶው በሚዘዋወርበት በወሳኙ የቀይ ባሕር በኩል የሚያቋርጡ የግዙፍ የጭነት መርከብ ኩባንያዎች መስመራቸውን እንዲቀይሩ አስገድዷል።

ምንም እንኳን በአሜሪካ የሚመራው የባሕር ኃይል ጥምረት አገራት በሁቲ ዒላማዎች ላይ የአየር ጥቃት መፈጸም ከጀመሩ አንድ ወር ቢያልፋቸውም፣ አማጺያኑ አሁንም በመርከቦች ላይ ከባድ ጥቃቶችን የመፈጸም አቅም እንዳላቸው አሳይተዋል።

ሁቲዎች በቀይ ባሕር ላይ በሚተላለፉ የምዕራባውያን መርከቦች ላይ የሚፈጽሙትን ጥቃት የሚያቆሙት፣ እስራኤል በጋዛ ሰርጥ ውስጥ በሐማስ ላይ የምታካሂደውን ወታደራዊ ዘመቻ ስታቆም መሆኑን አሳውቀዋል።

# ስፖርት




# ሱቱሜ አሰፋ የቶኪዮ ማራቶንን ክብረወሰን በማሻሻል አሸነፈች

**ቦጋለ አበበ**


ከአምስቱ የዓለማችን ታላላቅ የማራቶን ውድድሮች አንዱ የሆነው የቶኪዮ ማራቶን ትናንት ሲካሄድ ኢትዮጵያዊቷ አትሌት ሱቱሜ አሰፋ የቦታውን ክብረወሰን በማሻሻል አሸንፋለች።

የርቀቱ የዓለም እና የኦሊምፒክ ሻምፒዮኖች፣ የክብረወሰንና ፈጣን ሰዓት ባለቤቶች በሁለቱም ፆታ ጠንካራ ፉክክር ባደረጉበት የ2024 ቶኪዮ ማራቶን በርካታ ያልተጠበቁ ውጤቶች ተመዝግበዋል።

በሴቶች መካከል በተካሄደው ውድድር ቀደም ሲል የአሸናፊነት ግምት የተሰጣቸው በርካታ አትሌቶች የነበሩ ሲሆን ብዙም ትኩረት ያልተሰጣት የ29 ዓመቷ ሱቱሜ በድንቅ ብቃት ማሸነፍ ችላለች። የገባችበት 2:15:55 ሰዓትም የቶኪዮ ማራቶን የቦታው አዲስ ክብረወሰን ሆኖ ተመዝግቧል።

ኬንያዊቷ የቀድሞ የርቀቱ የዓለም ክብረወሰን ባለቤት የነበረችው አትሌት ብሪግድ ኮስጌይ 2021 ላይ 2:16:02 በሆነ ሰዓት የቶኪዮ ማራቶን ባለክብረወሰን የነበረች ሲሆን፤ በትናንቱ ውድድር ኢትዮጵያዊቷ ሱቱሜ ክብረወሰኑን በእጇ ያስገባችበትን ውጤት አስመዝግባለች። በዚህም በጃፓን ምድር በሴቶች ማራቶን ከ 2:16:00 በታች በመግባት የመጀመሪያዋ አትሌት መሆን ችላለች። በተጨማሪም ያስመዘገበችው ሰዓት የርቀቱ የዓለም ስምንተኛው ፈጣን ሰዓት ሲሆን 2022 ላይ በሲዖል ማራቶን ካስመዘገበችው የራሷ ፈጣን ሰዓት ከሁለት ደቂቃ በላይ የተሻለ ነው።

በውድድሩ ሱቱሜን ተከትላ ኬንያዊቷ ሮዝማሪ ዋንጂሩ ሁለተኛ ደረጃን በመያዝ ስታጠናቅቅ፤ የቡዳፔስቱ የዓለም ሻምፒዮና የማራቶን ባለድሏ ኢትዮጵያዊት አትሌት አማኔ ቦሪሶ ሦስተኛ ደረጃን ይዛ ውድድሩን ጨርሳለች።




**አትሌት ሱቱሜ አሰፋ የመጀመሪያ የማራቶን ድሏን ቶኪዮ ላይ አሳክታለች፣**

እንደ ርቀቱ የዓለም ሻምፒዮን አማኔ በሪሶ ትልቅ የአሸናፊነት ግምት ተሰጥቷት የነበረችው የኔዘርላንዷ አትሌት ሲፋን ሐሰን 2:18:05 በመግባት አራተኛ ደረጃን ይዛ ውድድሩን ፈፅማለች።

የመጀመሪያ የማራቶን ድሏን ያጣጣመችው ሱቱሜ ከውድድሩ በኋላ በስፍራው ለነበሩ ጋዜጠኞች በአስተርጓሚ በሰጠችው አስተያየት "እጅግ በጣም ደስ ብሎኛል፣ ደስታዬን ለመግለፅ ቃላት ያጥሩኛል፣ ይህ የመጀመሪያ ድሌ እንደመሆኑ ደስታዬ ወደር የለውም" በማለት ተናግራለች።

ጠንካራ ትንቅንቅ በታየበት የወንዶቹ ውድድር ኬንያውያን አትሌቶች ከ 1ኛ እስከ 3ኛ ያለውን ደረጃ ይዘው በማጠናቀቅ የበላይነት ይዘዋል። በውድድሩ ኬንያውያን በበላይነት ያጠናቁ እንጂ ለአሸናፊነት የተጠበቀው የቀድሞው የርቀቱ የዓለም ክብረወሰን ባለቤት ኤሊድ ኪፕቾጌ 10ኛ ደረጃን ይዞ ማጠናቀቁ ያልተጠበቀ ውጤት ሆኗል።

ቤንሰን ኪፕሩቶ የዘንድሮው የቶኪዮ ማራቶን ባለድል ሲሆን በውድድሩ ጠንካራ ተፎካካሪ መሆን ያልቻለው የሃገሩ ልጅ ኪፕቾጌ ይዞት የነበረውን የቦታውን ክብረወሰን በ24 ሰከንድ በማሻሻል 2:02:16 ሰዓት አሸናፊ መሆን ችሏል።

በ2021 እና 2022 የቦስተን እና ቺካጎ ማራቶኖችን ያሸነፈው ኪፕሩቶ፤ ቶኪዮ ላይ የገባበት ሰዓት 2:02:16 በማራቶን ታሪክ የምንግዜም 5ኛው ፈጣን ሰዓት ሆኖ ተመዝግቧል።

ሌሎቹ ኬንያውያን ቲሞቲ ኪፕላጋት እና ቪንሰንት ንጌቲች 2ኛ እና 3ኛ ደረጃን ይዘው ውድድሩን ጨርሰዋል። ኃይለማርያም ኪሮስ እና ጌታቸው ፀጋዬ 4ኛ እና 5ኛ ደረጃን ይዘው ያጠናቀቁ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ሆነዋል።

የሁለት ጊዜ የኦሊምፒክ የማራቶን ሻምፒዮኑ ኤሉድ ኪፕቾጌ በ2024 የመጀመሪያ ውድድሩ ከ20 ማራቶኖች በኋላ ዝቅተኛ የተባለውን 10ኛ ደረጃ 2:06:50 በሆነ ጊዜ አጠናቋል። በቅርቡ የማራቶን የዓለም ክብረወሰኑን በቅርቡ በመኪና አደጋ ሕይወቱ ባለፈው ሌላኛው ኬንያዊ አትሌት ኬልቪን ኪፕቱም የተነጠቀው የ39 አመቱ ኪፕቾጌ ትናንት ያስመዘገበው ውጤት በስኬት የተሞላው የማራቶን ዘመኑ መጨረሻ እንደተቃረበ ማሳያ ነው ተብሏል።

በሦስት ተከታታይ ኦሊምፒኮች በማራቶን ወርቅ በማጥለቅ በታሪክ የመጀመሪያው አትሌት ለመሆን እየተዘጋጀ የሚገኘው ኪፕቾጌ ለፓሪስ 2024 ኦሊምፒክ እየተሰናዳ በሚገኝበት ወቅት ቶኪዮ ላይ ያልጠበቀው ውጤት ነው የገጠመው። "የሆነው ነገር ሆኗል፣ ሁሌ ፋሲካ የለም" ሲል የምንጊዜም የርቀቱ ኮከብ አትሌት ኪፕቾጌ ከውድድሩ በኋላ አስተያየቱን ሰጥቷል።

"ለውድድሩ ብቁ ነበርኩ፣ አንዳንዴ በውድድር መሐል ላይ እንዲህ አይነት ነገር ይፈጠራል" ያለው ኪፕቾጌ ከስድስት ወራት በኋላ ስለሚካሄደው የፓሪስ ኦሊምፒክ ለመናገር ጊዜው ገና ቢሆንም ከትናንቱ ውድድር በኋላ ወደ ሀገሩ ተመልሶ በቂ ዕረፍት ካደረገ በኋላ ወደ ልምምድ እንደሚመለስ ገልጿል።